# የሰይጣን መፈክር በዋሽንግተን ዲሲ ቅድስት ማርያም ቤተ መቅደስ

**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**

nigatuasteraye@yahoo.com

**ታህሳስ ፳፻፫ ዓ.ም.**

*የባንዲራ መቃጠል፥ የዳርድንበር መፍረስ፥ በጎሳና በቋንቋ መለያየት፥ ከኢትዮጵያዊው ፊደል ተሸሽቶ የላቲንን ፊደል ማስፋፋት ሲአስገርመን፥ የላቲን ሕገ ሃይማኖት አስፈላጊና ዓይን ገላጭ ስለሆነ አሁን ብንቀበለው የሚያስፈራን የለም ተብሎ በዋሽንግተን ዲሲ ቅድስት ማርያም ቤተ መቅደስ የቅኝ ግዛት ፖሊሲ በግልጽና በድፍረት ተሰበከ::*

## ማውጫ

መግቢያ ........................................................................................................1
መቅድም ........................................................................................................2
ክርስትናን የሚደመስሰውን ፒላጊዮስን ለተምታታ ‘ምሳሌነት’ ማቅረብ ........................................6
፩ኛ፡- “ጥንተ አብሶ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አላገኛትም” ..........................................9
፪ኛ “ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት” በሊቃውንት ጉባዔ ተመርምሮ የጸድቀ ማስመሰል ...........................10
በአቡነ ጳውሎስና በሚመሩት ሲኖዶስ በ‘ጥንተ አብሶ ዶግማ’ ስም ........................................11
እመቤታችን ከሰው የተለየችው ከሐናና እያቄም ‘ያለጥንተ አብሶ’ ተጸንሳ በመወለዷ አይደለም ........13
የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አባቶች ምስክርነት፡- ..........................................................15
፫ኛ. ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. ነጻ ስለሆነች ነገረ መለኮት ከኦሬንታል አቻወቿ የማትጋራ ማስመስል......................16
፬ኛ ራሱ ‘መናፍቅ’ ሆኖ ሳለ ሌላውን ‘መናፍቅ’ ወይም ‘ጎራ (cult)’ ብሎ ስድብ አዘል ምክር ለጋሽ መሆን ........................................................................................................19
፭ኛ “አንዳንድ ምዕመናን ካህኑን አይሰሙትም”ይላል ..........................................................23
አባቶቻችን በደፍተሮች ላይ የወሰዱት የተቀደሰ ርምጃ፡- ................................................24
፮ኛ የጣሊያንን ‘ማሪያማዊ ሕጉ ሃይማኖት’ እንከተል እያለ የተዋህዶውን ሕገ- ሃይማኖት ባዕድና መሳለቂያ ያደርጋል አለ።........................................................................................................28
ማጠቃለያ ........................................................................................................31

# መግቢያ

በአገር ውስጥ የሚኖረው በውጭም የተበተነው ወገናቸው ስለአገራችን፥ ስለታሪካችንና በጥቅሉ ስለምንርባት ዓለምና አካባቢያችን እንድንማማርባቸውና እንድወያይባቸው በጥልቀት ያሰቡ ወገኖቻችን በዘረጉልን ድኅረ ገጾች በኅዳር ወር "ጠልሰም በዲሲ (እዚህ ላይ በመጫን ያንብቡ)" በሚል ርእስ ያዘጋጀኋት ጦማር በሰፊው ተነባለች፡፡ በመላ ዓለምና በአሜሪካ ዙሪያ፥ በተለይም በጠልሰሚ የተንጸባረቀውን ሽፍጥና ክህደት በቅርቡ የሚያውቀውን የዋሽንግተን ዲሲ ሕዝብ ከተጠበቀው በላይ በአመርቂ ሁኔታ ማርካቷን ከያቅጣጫው ከደረሰኝ የይበል ድጋፍ በሰፊው ተገንዝቤአለሁ፡፡

በጠልሰመኛው የተዘጋጀችው ጠልሰም ታሪክን ደምስሳ፥ እምነትን አቃውሳ፥ ቤተ ክርስቲያናችን ከኦሪየንታል አቻዎቿ ለይታ፥ በወጣቶች ላይ አተኩራና እግር መንገዷንም በስማ በለው ለካንሳስ ደብረ ሣህል መድኃኔ ዓለም ምእመናንን ልምከራችሁ እያለች በሰነዘረችው አዋጅ ያፍዝ ያደንዝዝ አዚም ለማዞር መሞከሯን ያነበባት ወገን ሳይታዘባት እንዳልቀረም ተረድቻለሁ፡፡

ያፍዝ ያደንዝዝ አዚሟን "ጠልሰም በዲሲ ደፍተራ" ብየ ባቀረብኳት ጦማር ብቻ ማካተት ስላልተቻለ፥ ይህችንና ሌሎችንም ተከታታይ ጦማሮች ማዘጋጀት ተገደድኩ፡፡ ጠልሰመኛው ከቤተ መቅደስ ለቆ እስኪወጣ ድረስ፥ ጠለሰሚ የጸንሰቻቸው በተለያዩ ርእሶች ገና የሚወለዱ ብዙ የማቀርባቸው ተከታታይ ጦማሮች አሉ፡፡ ከነሱም ውስጥ አንዷ የክርስቶስን ወደዚህ ዓለም ለኃጢአት ሥርየት መምጣቱን የካደውን ፒላጊዎስን በጠቀሰችባት አንቀጿ ሰውን ሁሉ ለማሳሳት የሞከረችበትን መፈክረ ሰይጣን የምገልጽባት ይህች ጦማር ናት፡፡

በአገራችን ውስጥ ስላሉት ለነገረ መለኮቱ መሠረትና መለኪያ ሆነው ስለማይጠቀሱ መጻሕፍት በመቅድሟ ገልጬ፥ ሐሰተኛው መንፈሳዊ ጠላት አዳምንና ሔዋንን በስማ በለው እንዳሳታቸው ሁሉ፥ ጠልሰመኛውም በዲሲ ቅድስት ማርያም ቤተ መቅደስ ውስጥ ቆሞ፥ ከገጽ 208 እስከ 209 ከ ፩ እስከ ተራ ቁጥር ፺ "አለባቸው፤ ይገባቸዋል"፥ እያለ በስማ-በለውና ባሽሙር ለከንሳስ መድኃኔዓለም ምእመናን ለመንገር ያሰራጨውን የክሕደትና የሐሰት መፈክር ከአንባቢ ጭንቅላት ጠራርጎ ለማስወጣት የማቀርባቸውን የአንቀጾችን ዝርዝር ከዚህ በታች እገልጻለሁ፡፡

፩ኛ *"ጥንተ አብሶ እመቤታችን ቅድስ ድንግል ማርያም አላገኛትም" የሚለው የነገረ ማርያም ይትበሐል አስተርአየ ጽጌ እንደሚፈርጁት ዘመን አመጣሽ ሳይሆን ጥንታዊ መሆኑን መገንዘብ አለባቸው"*

፪ኛ *"ዶግማው በኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባዔ ተመርምሮና ጸድቆ በጽሑፍ የታወጀ ሕገ ሃይማኖት መሆኑን ማወቅ አለባቸው"*

፫ኛ *"ቤተ ክርስቲያን የራሷ ቅዱስ ሲኖዶስ ያላት ነጻ ቤተ ክርስቲያን እንደ መሆኗ በሃይማኖትም ሆነ በሌላ ረገድ የኮፕቲክ ቤተ-ክርስቲያን ታዛዥ እንዳይደለች ማስታወስ ይገባቸዋል"*

*፬ኛ “ውጉዝ ካህን በመከተል በአሉት ላይ ሌላ የመናፍቅ ጎራ (cult) ከመፍጠር በስተቀር የሚጠብቁትና የሚያስጠብቁት እምነትና ትውፊት እንደሌለ በጥሞና ሊረዱት እንደሚገባ መገንዘብ አለባቸው” ውጉዝ ካህን በመከተል ላይ ሌላ የመናፍቅ ጎራ”*

*፭ኛ “የጠለቀ የነገረ ሃይማኖት ትምህርት የሌላቸው ሰባኪዎችና የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች. . . . ከሊቃውንት ጉባዔ ፊት ከቀረቡ በኋላ ስሕተታቸውን አምነው በትምህርትና በምክር ተመልሰዋል”*

*፮ኛ “በሃይማኖት ሽፋን የቆየ ቁርሾውን በመወጣት ጊዜውን ከሚያባክን መናፍቅ ይልቅ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በትክክል የሚፈጽም በመንፈሳዊ አቋሙም ጥርጥር የሌለበት ካህን መፈለግ ጠቃሚ መሆኑን ሊያውቁ ይገባል”*

# መቅድም

ቅዱስ መጽሐፍ “የተጻፈ ሁሉ ለተግሳጽና ለምክር ተጻፈ”(ሮሜ ፲፭፡፬) እንዳለው፥ ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ድረስ ባሉት መጻሕፍት “ሁሉ” አለባቸው። በግፍ የፈሰሰው የአቤል የደም ድምጽ ጩኸት እንዳለበት፥ “በምድር ላይ ኮብላይና ተቀበዝባዥ እሆናለሁ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል” (ዘፍ ፬፡፲፬) እያለ የጮኸው የወንድም-ገዳዩ የቃኤል ጩኸትም አለበት። የበልአም በረከትና መርገምም ጎን ለጎን አሉበት። የሰብአዊ ሞትን መርዶ የተሸከመው የዲያብሎስ ድምጽ እንዳለበት ሁሉ፥ የሰብአዊ ሕይወትን የምሥራች የተሸከመው የቅዱስ ገብርኤል ድምጽም አለበት። የእባቡ ድምጽ እንዳለበት፥ የበልአም አሕያ ድምጽም እንደዚሁ። እናትና አባቶቻችን የመጽሐፍ ቅዱስ ይዘት ይህ እንደሆነ እያወቁ፥ የሁሉ ባለቤትና ሁሉን አሸናፊ የእግዚአብሔር ድምጽና ስም ስላለበት ኃያል ፀባዖት ቅዱስ እያሉ ከምዕራቡ ዓለም አቀባበል ከፍ ባለ ክብር ተቀብለውታል። እንድንገሰጽባቸውና እንድንመ

ክርባቸው ከመጽሐፈ ሄኖክ ጀምሮ እስከ ትንሺ ልፋፈ ጽድቅ ጎን፥ ለነገረ መለኮት መለኪያነት የማይጠቀሱ ሌሎችንም እስከ ጠልሰማ-ጠልሰሞች ድረስ ያሉትን መጻሕፍት አስቀምጠዋቸዋል። “ሁሉ” የምትለው ቃል በተስማሚና በተቃራኒ የተጻፉትን ሁሉ መጻሕቶችና ኩርባብኞች የምታጠቃልል ናት።

ቅዱስ መጽሐፍ ግድያን እየተቃወመ ገዳይንና ተገዳይን፥ ውሸትን እየተቃወመ ውሸትንና (የሰኢራ የውሸት አውንታ የሃ.ሥ. ም፭ ቁ.፬) እውነትን እንዳሰፈረ፥ የቀደሙ አባቶቻችን ጠልሳሚዎችንና የጠልሰምን ይዘት እየተቃወሙ “የተጻፈ ሁሉ ለተግሳጽና ለትምህርት ተጻፈ” ያለውን ለመጠበቅ ጠልሰምን ጨርሰው ሳያጠፏት በልፋፈ ጽድቅ (በፍካሬ ኢየሱስ) ጎድን አስቀምጠዋታል። የአገራችንን የሩቅ ዘመኗን ጉዞና የሕዝባችንን የመንፈስ ዕድገት ርከን ስለሚያስረዳን የሁሉም ጎን ለጎን መኖር መልካም ቢሆንም፥ የሊቃውንቱ ኃይል የጠፋባት ዘመን እንደ አሁኑ ሲከሰት፥ ጠልሰመኞቹ “ማርያማዊ ሕገ-ሃይማኖት” እና የመሳሰሉትን እየጨማመሩ በራሳቸው ተሸክመው በደረታቸው አንግበው በቤተ መቅደስ ብቅ ይላሉ።፥ የጠራውን የተዋሕዶ ኦርቶዶክስን ትምህርትና እምነት ይሸፍኑታል። ሰይጣን በገሐድ ከሚመለከበት አገር ወደ አገራችን ለሚመጡት ሚሲዮኖች ትችት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንንም

አጋልጠው ይሰጧታል። የሁሉም ጎን ለጎን መቀመጥ ባለመገንዘባቸውና የጠራዉን ነገረ መለኮት ባለመረዳታቸው፥ እንዲሁም የውጩን ተጽእኖ መቋቋም አቅም የሚያጥራቸው ወገኖቻችንም፥ ከውጭ ከመጡት ባእዳን ጋራ በመተባበር በራሳቸው እምነት፥ ታሪክና ቤተ ክርስቲያን ይዘምቱባቸዋል።

ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ቲቶ “እለ ርቱዕ ይፍጽምዎሙ አፉሆሙ እስመ እለ ይገፈትኡ አብየተ ኩሉ፡ ወይሜህሩ በዘኢይደሉ በዘይረብሆሙ ኀሳረ፡፡ .... በእንተ ዝንቱ ተዛለፎሙ ምቱረ ከመ ይጠይቁ በሃይማኖት። ወኢያምጽኡ መኃድምተ ወሥርአተ ሰብእ ዘይመይጣ ለጽድቅ”(ቲቶ ፩፡፲፩-፲፬) ማለትም፡- “ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ በየቤቱ እየዞሩ እውነትን ወደሐሰት የሚለውጥ የተሳሳተ ሥርአት የሚያመጡትን አፋቸውን መዝጋት ተገቢ ነው። ምእመናንም እነሱን የሚሰብኩትን በመስማት ከኦርቶዶክስ (ቀጥተኛ) ሃይማኖት እንዳይወጡ ጠንክረህ አሰተምር” የሚለውን ወሳኝ ትእዛዝ መሠረት በማድረግ፥ የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ ፍትሐ ነገሥቱም “ወለእመ ኮነ መፍቅድ ኀበ ፍድፋዴ አዕምሮ መጻሕፍት በምክንያተ አስተርዕዮተ ዕልዎታት ይሢምዎ ለማዕምረ መጻሕፍት”(ፍ.ነ አንቀጽ ፬፡ ቁ. ፷፱) ይላል። ማለትም፡-“የክሕደትን ብዛትና ኃይል ለመቋቋም መጻሕፍትን አብዝቶና ጠልቆ የተማረውን ይሹሙ” የሚለውን ትእዛዝ አፍርሰው በጥቅማ-ጥቅም ድለላ የሰገሰጉና የተሰገሰጉ ቀሳውስት፥ መነኮሳት፥ ሰባኪዎች ጳጳስት፥ ደፍተራ-ገለፈቶች ለዚህ ሁሉ ቀውስ ተጠያቂዎች ናቸው። ሊቃውንት አበው፥ ታሪክ እያቃወሰ ሕዝብ እያስለቀሰ እየዋሸና እየቀጠፈ አገር ከሚመራ ጋራ የሚስማማውን ጳጳስ ”አሆ በልዎ ለእግዚአብሔር ወእንብየ በልዎ ለጋኔን ወይጎይይ እምኔክሙ”(ያዕ ፬፡፯) ማለትም፥ ከእግዚአብሔር ፈቃድ፥ ከሕዝብ ስምምነት ውጭ በኃይል ልምራ ከሚል አላዊ(ከሐዲ) መሪ ጋራ ለመተባበር ነገረ መለኮቱን ያሚያፈርስ፥ ሕዝብ የሚያስለቅስ ጳጳስ መናፍቅ መሆኑን ተረድተህ አመራራቸውን አትቀበል። ትእዛዛቸውን እንቢ ብል እያሉ ነው፥ ሊቃውንት አበው፥ በጉባዔያቸው ያስተማሩኝ።

ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመወረር የተጠቀመባቸው ነገሮች፥ የአገሪቱን ድንበር ማፋለስ፥ ሕዝቡን በዘር፥ በጎሳ፥ በቋንቋና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ነገረ መለኮት ነቅሎ የራሱን ነገረ መለኮት በነ አቡነ ጴጥሮስ ልብ ላይ መተከል ነበር፡፡ ሆኖም በዚያ ወቅት በመላ ኢትዮጵያ የነበሩ ሊቃውንት አበው “ወእንብየ በልዎ ለጋኔን” የሚለውን እያስተማሩ ከጀግኖች አርበኞች ጋር በግንባር ተሰለፉ፡፡ የሸበል፥ የበረንታና የለምንጩን ሊቃውንትም፥ “እኸ እንቢ በል”! እያሉ የበላይ ዘለቀን የሞራልና የመንፈስን ልዕልና ወደ ሰማይ ተኮሱት! የቅኔ፥ የመጻሕፍት መምሕራንም፥-

“ሂጅ ተመለሺ ግቢ አገርሽ ቅኔ፥

ወንዶች በዋሉበት መዋሌ ነው እኔ”

እያሉ በመቀኘት ጉባዔያቸውን እያጠፉ ከጀግኖች ጋራ ተቀላቀሉ። ሕዝቡም “አሆ በልዎ” የሚለውን ወደ አማረኛ ተርጉሞ “እሽ በል”!!! በሚል ሆታ በላይ ዘለቀን እየተመመ ተከተለው። ”ወእንብየ በልዎ ለጋኔን“ የሚለውን ወደ አማረኛ ተርጉሞ “እኸ እንቢ በል!” እያለ የኢትዮ’ጵያን ህዝብ ንቆ ለመውረር የመጣዉን ጣሊያንን አዋርዶ ምልምል ግንዱን በአለም መድረክ ላይ አቆመው።

እነዚህ ሁሉ ጀግኖች ላተረፉት ታሪካዊ፥ ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ውለታ እንደ አቡነ ጴጥሮስ የሚታይ ሐውልት ባይቀረጽላቸውም፥ ታሪካዊ ዝናቸው በየተወለዱበት መንደር የተተካው ትውልድ በቃልና በእንጉርጉሮ እየተቀባበለው በሁላችንም ጆሮ ፈሷል። ጣሊያን አገሪቱን ለመውረር የተጠቀመባቸውን ዘዴዎች ሁሉ አንድም ሳይቀር ያቶ መለሰ መንግሥት ተጠቅሟል። ባንዲራ አቃጥሏል። ድንበር አፍርሷል፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ ወደብ አልባ አድርጓል። ዓለም የሚያደ ንቀውንና የሚያኮራውን ፊደል ነቃቅሎ ጥሎ የላቲኖችን ፊደል እንዲስፋፉ አበረታቷል። በሃይማኖትም *“የላቲኖችን እንቀበል”* የሚሉ እንደ ደፍተራ ገለፈት ያሉትን ጠልሰመኞች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በቤተ መቅደሳችን አሰማርቷል።

አገራችን በረዥሙ የታሪክ ዘመኗ የውጭም ሆኑ፥ አገር በቀል መሪዎች፥ ደፍተራ-ገለፈቶችንና ጠልሰመኞችን በመሣሪያነት እየተጠቀሙ ጊዜን ተንተርሰው በመከሰት፥ በኀብረታቸው የሚፈጸሟቸው ደባዎች የታሪክ አንጓዎች ናቸው። በነዚህ የታሪክ አንጓዎቻችን ኢትዮጵያ ግርዱን ከገለባው፥ ምርቱን ከእንክርዳዱ የለየችባቸው፥ እውነተኛ ልጆቿን ከእንጀራ ልጆቿ ለይታ የታዘበችባቸው፥ ቤተ ክርስቲያናችንም እውተኞችን ካህናት ከምንደኞች ለይታ ያወቀችባቸው መስተዋቶች ናቸው።

በኬንያ፥ በዩጋንዳ፥ በታንዛንያና በሄድኩባቸው አገሮች የማይገኙ ኢትዮጵያን የምሥራቋ ኮከብ እንድትባል ያደረጓት፥ ቤተ ክርስቲያናችን በእቃ ግምጃ ቤቷ ጎን ለጎን ያስቀመጠቻቸው የሃይማኖት የስነ ጽሑፍ የባህልና የአዕምሮ እድገት ምንጭ የሆኑን የተለያዩ መጽሐፎች ናቸው። በእነዚህ በሰበሰበቻቸው መጻሕፍት ክፉውንና ደጉን ለይቼ እንዳውቅ ቀርጻ ከማሳደጓ ባሻገር፥ ወደውጭም ወጥቼ እንድማር ያደረገችኝ ስለሆነ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እናቴ፥ መኩርያና ስንቄ መሆኗን ተረድቻለሁ። በአጸደ ነፍስና፥ በአጸደ ሥጋ ካሉት ሊቃውንት አበው፥ እንዲሁም በየዋሕነትና በገርነት ቤተ ክርስቲያናችንን ከሚሳለሟት እናትና አባቶች የበለጠ እምነት፥ ብቃትና ለቤተ ክርስቲያናችን ፍቅር አለኝ ባልልም፥ ከማነኛውም ጠልሰመኛ የበለጠ እምነት፥ ብቃትና ለቤተ ክርስቲያኔ ፍቅር እንዳለኝ አምናለሁ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፥ ከሕጻንነቴ ጀምሮ በእንተ ስማ-ለማርያም እያልኩ የዕለት ምግቤን እያገኘሁ በመማር በአደግኩት ላይ፥ ስለ እመቤታችን ግንዛቤ የሌላቸው ቃጭል ለማቃጨል ወደ ቤተ መቅደስ የገቡ ሰዎች ማርያምን ካደ እያሉ በኔ ላይ የፈጸሙትን የሐሰት ዘመቻ ሳይ፥ ጌታችን በእለተ ስቅለት በደረሰበት መከራ “በዝ ዕጽ ርጡብ ከመዝ ገብሩ፥ እፎኑመ ይከውን በይቡስ” (ሉቃስ ፳፫፡፴፩) እንዳለ፥ ማለትም፥ መለኮት በተወሐደው በእኔ አካል ላይ ይህን ሁሉ ፈተና ካደረሱብኝ፥ በሌሎችማ ምን ያህል የከፋ ይሆን?” እንዳለው፥ እነ ደፍተራ ገለፈቶች ከኔ ይልቅ በእጥፍ እጥፍ በበለጡት በሰንቶቹ ሊቃውንት ላይ ምን ያህል የከፋ ፈተና ፈጽመዋል? በፈጠሩባቸው የሐሰት ስም ማጥፋት ዘመቻስ ስንቶች ተበትነዋል? የሚሉና የመሳሰሉት ጥያቄዎች እየመጡብኝ ነው። ቤተ ክህነቱን ወክዬ በአገልግሎቱ እሳተፈው የነበረው የሃይማኖት አበው አባላት ድርጅቱን ዘግተው ወደተለያዩ የእምነት ድርጅቶች ተበታተኑ ሲባል ሰምቼ አዝኘና ፈርጀባቸው ነበር። አሁን ግን ከሀገር ርቀው ባሉት በአቡነ መልከ

ጼዴቅ፥ በአባ መአዛና በራሴ ላይ የደረሰውን የሐሰት ዘመቻ ስመለከት ፍርድ የሰነዘረባቸው ሕሊናየ የጸጸትና የይቅርታ እንባየን አፈሰሰላቸው::

ሌሎችም በቤተ ክርስቲያናችን ተጠምቀው ያደጉ እንደ ሃይማኖተ አበው አባላት በተፈጸመባቸው ዘመቻ ወደሌላ ድርጅት እየጣሉ የሄዱ ወገኖቻችን፥ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነትና ትምህርትን ጠንቅቆ አውቆ በዓላማው የጸና ካህን ቢያገኙ ኑሮ፥ ጥለው ከመሸሽ ይልቅ፥ እኔ እነ አቡነ ማትያስንና ተከታዮቻቸውን ከተፋለምኩበት መፋለም በበለጠ ሁኔታ ይፋለሟቸው እንደ ነበረ ጥርጥር የለኝም። <u>አሁንም ቢሆን ነገረ መለኮቱን ሳታቃውሱ በነዚህ ዘመን አመጣሾች ዘመቻ እያዘናችሁ የተበተናችሁ ሁሉ ወገኖች ፊታችሁን ወደ የኢትይጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችሁ እንደትመልሱ እማጸናችኋል።</u>

ከዚህ በፊት ያቀረብኳቸው ጦማሮች የነኳቸው ሁሉ፥ ለነገረ መለኮቱ መቃወስ፥ ለታሪክ መደምሰስ ለቤተ ክርስቲያናችን መፍለስ ምንም ሳይሰማቸው፥ ስማቸው በመጠቀሱ ብቻ የተቁነጠነጡ ሰዎች እንዳሉ ታዛቢ እየተነጋገረበት ነው። ሌሎችም የተሳሳተውን ትምህርት በመዝሙርም፥ በካሴትም ሲያሰራጩ የነበሩ ሁሉ ግለሰቦችም፥ በራሳቸው ፈጠራ ሲያሳስቱ መኖራቸውን ለመሸፈን *"አባቶቻችን ተሰደቡብን"* የሚል ድምጽ ማሰማትን እንደጀመሩ ያያቸውና የሰማቸው ሁሉ እየታዘባቸው ነው።

ጠልሰሚንና እኔ ያቀረብኩትንም ጦማር ጎን ለጎን አንብባችሁ የተረዳችሁ ሁሉ፥ ከራሴ አፍልቄ ከጠልሰሚ ርቄ አንዳች የስድብ ቃል እንዳልተናገርኩ ምስክሮቼ ናችሁ:: መንፈሳችሁ የጦማሯን ይዘት ከተቀበለው፥ ጠልሰመኞች ለግል ጥቅምና ክብራቸው፥ ሌሎቹ የነሱ ጀሌዎች ገብቷቸውም ሆነ ሳይገባቸው የጠልሰሚንና የጦማሬን አቅርቦት አበላሽተውና መልካቸውን ቀይረው በማቅረብ አንባቢን የሚያደናብሩትን በመገሰጽ፥ ያልተረዳውን እንዲረዳ በመርዳት እንድትተባበሩኝ የታሪክ፥ የሃይማኖትና የሞራል ግዴታ አለባችሁ::

የግል ዝናንና መረግረግን ሳያስቀድሙ፥ ለእምነቱና ለታሪካችን ቀጥ ብለው የቆሙትን የከንሳስ መድኃኔ ዓለምን ምእመናን እግዚአብሔር ባያዘጋጅልኝ ኖሮ ጠልሰመኞች በፈጸሙትና አሁንም በሚያካሄዱት ዘመቻ፥ እንደ ሌሎች ወገኖቻችን፥ ወደ ሌላ እምነት ክልል ባልገባም፥ አሁን በየድኅረ ገጾች የሚሰማው ድምጽ ሁሉ እንዲህ በፈጠነ ሁኔታ ባልተሰማም ነበር። *"ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት"* የተባለችው ጠልሰም ከዲሲ ቅድስት ማርያም ቤተ መቅደስ ብቅ ባለችበት ወቅትም፥ የተበሳጩ ወገኖቻችን ባይልኩልኝ ኖሮም "ጠልሰም በዲሲ ደፍተራ" የተሰኘችው ጦማር ከእኛ ከንሳስ መድኃኔ ዓለም ቤተ መቅደስ ባልመነጨችም ነበር። "ጥቂት የሃይማኖት ትምህርት የሌላቸውን ሰብስበው ኑፋቄአቸውን ያስጠናሉ" ገጽ 208:: የሚለውን የደፍተራ ገለፈትን ትብትብ አብራርቼ ለመግለፅ ይህችን ጦማር ለማዘጋጀት ባልበቃሁም ነበር። በሃይማኖታቸው ጸንተው ከጎኔ ያልተለዩትን ሁሉ እያመሰገንኩ *"ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት"* በሚል ስም የተዘጋጀችውን "ጠልሰም" አዘጋጇን ጠልሳሚ ብየ እንደሰየምኩ፥ አሁን ደግሞ ጠልሳሚውን ደፍተራ ገለፈት፥ ጠልሰሚን "መፈክረ ሰይጣን" ብየ ሰይሜያቸዋል።

ጠልሳሚዋን *"ደፍተራ ገለፈት"* ጠልሰሚን መፈክረ ሰይጣን ብየ የሰየምኩበት ምክንያት፥ ራሱ በጠለሰመው ጠልሰም ስለ ሴቶች ክብረ ንጽህና ሲናገር፥ ሴቶች የሚወልዱት "የአባለ-ሩካቤ ገለፈት ከተበጠሰ በኋላ መሆኑ የታወቀ ነው"ገጽ 51: ብሎ ጸያፍ ቋንቋ በመጠቀሙ ከራሱ ጠልሰም ስላገኘሁት እሱ ራሱ ይጠራበት ብየ ነው:: ይህ አይነት አነጋገር በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አውደ ምሕረት ላይ ጽፎ ማሰራጨት ይቅርና፥ በጠቅላላው ባሕላችን የሴቶች ክብረ ንጽሕና የሚገለጸው ንጽህናንና ቅድስናን በሚገልጹ ቃላት ነው:: በድንግልና ያሉትንና በዚህ መስመር ያለፉትን ሴቶች ሁሉ ቅዱሳት እንላቸዋለን:: እመቤታችንንም የደናግል መመኪያ እያልን የምናቀርብላት ምስጋና የነሱ ሁሉ አክሊላቸው ነሽ እያልን ነው:: ለማነኛዋም ክብሯን ለጠበቀች ድንግል እመቤት የሚነገረው "ክብረ ንጽህና" ተብሎ እንጅ ገለፈት በሚል ቃል አይደለም:: እሱ ግን ከውጭ በቀላወጠው ግንዛቤ በገጽ 51 ላይ ፈጥሮ "ገለፈት" አለው::

ጠልሰሚን መፈክረ ሰይጣን ያልኩበትም፥ ጌታችን "ሐሰተኛ የሐሰት አባት. . . እውነት በሱ የለም"(ዮሐ ፰፡፵፬):: እንዳለው፥ የሐሰት አፍላቂ ሰይጣን እንደሆነ የተረጋገጠ ነው:: ደፍተራ ገለፈትም የዲሲ ቅድስት ማርያምን ቤተ መቅደስ ተጠቅሞ፥ በኢትዮጵያውያን ወጣቶችና በከንሳስ መድኃኔ ዓለም ምእመናን ላይ አተኩሮ የሱን ስማ-በለው በሰማ ሁሉ ላይ ሐሰትን (መፈክረ ሰይጣን) እያፈለቀ በማሰራጨቱ ነው:: *"ጥንተ አብሶ ዘመን አመጣሽ ሳይሆን ጥንታዊ መሆኑን መገንዘብ አለባቸው"* እያለ በወጣቶችና በከንሳስ ምእመናን ላይ ያነጣጠረውን የሃይማኖትና የታሪክ ክህደት *"ምን ሲወጉ፡ ምንን ይጠጉ"* እንደሚባለው፥ ነገረ መለኮቱን ለማፍረስ ታሪክ ለማቃወስ የርዕሰ አድባራት የዲሲን ቅድስት ማርያም ቤተ መቅደስ ጥግ አድርጓል:: ደብሯን ከርዕሰ አድባራትነቷ አውርዶ፥ ቤተ መቅደሱንም የሐሰቱ (የመፈክሩ) ማሰራጫ በማድረጉ ነው::

*"ስደት ለውሸትና ለእምቢተኛነት አመች ሆኖ ስለተገኘ ሥርአተ ቤተ ክርስቲያን ለመጠበቅ አስቸጋሪ ሆኗል"* 209:: እያለ የተናገረውን ዘበት ለኢትዮጵያውያን ሁሉ እዩልኝ ተረዱልኝ እያልኩ፥ እሱን ይገስጻል፥ ለአንባቢም የእውነት ፍንጭ ይሰጣል ብየ ስላሰብኩ፥ ከተናገራቸው አንቀጾች ሳልወጣና ሳልወርድ እውነቱን ለመግለጽ በፒላጊዮስ (Pelagius) እጀምራለሁ::

# ክርስትናን የሚደመስሰውን ፒላጊዮስን ለተምታታ 'ምሳሌነት' ማቅረብ

*"በውርስ ኃጢአት የምታምን ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፒላጊዮስን ባወገዘችው ጊዜ የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን መጠለያ ሰጥተዋለች፥ ይህም በትምህርቱ መስማማቷን ያሳያል"* 90:: ይላል:: ከ(346—432 ዓ.ም.) እንደኖረ የሚነገርለት ፒላጊዮስ (Pelagius) ምን ያህል የክርስትናን መሰረት የሚያናጋ ፍልስፍና እንደነበረው ለማወቅ (እዚህ ላይ በመጫን ያንብቡ)::

**ሀ.** የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስ ለኃጢአት ሥርየት መሞቱን ያምናሉ ያስተምራሉ:: የሁሉም መጽሐፈ ቅዳሴያቸው ከፒላጊዮስ ፍልስፍና ፈጽሞ የራቀ ነው:: ለመሆኑ የትኛዋ ናት ከኦሬንታልም ሆነ ከባዛንታይን አብያተ ክርስቲያናት የፒላጊዮስን ትምህርት የተቀበለችው? በራዕይ ም፲፫፡ ቁ፮ ላይ የሰይጣን ዋሾነት ለመግለጽ "አብቀወ አፉሁ" የሚል ሐረግ አለ:: ሊቃውንት "ውሸቱን ለቀቀው" ብለው ይተረጉሙታል:: እኔም በዚህች ጦማር በየአንቀጹ የደፍተራ ገለፈትን ዋሾነት ለመግለጽ "ውሸቱን ለቀቀው (አብቀወ አፉሁ)" በማለት ከዚህ እጀምራለሁ::

**ለ.** ፒላጊዮስ "የአዳም ውድቀት ግላዊ የሞራል ውድቀት ነው፡፡ ስለዚህ የሞራልን ምንጭ ለይቶ ለማወቅ የማይችሉ ሕጻናት አዳም በምርጫው ከመውደቁ በፊት ከነበረው ባህሩዩ ስለሚመሳሰሉ የወርስ በደል የለባቸውም" ብሎ በማመኑ የፒላጊዮስ አመለካከት ከክርስትና ትምህርት ጋር ይጋጫል:: ስለዚህ አብቀወ አፉሁ!

- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በአንድ ሰው ኃጢአት ወደዓለም ገባ . . . በአዳምመተላለፍ ኃጢአት ባልሠሩት ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ" (ሮሜ ፭፡፲፪-፲፬)
- "እስመ ኀጉላን ንሕነ በኃጢአት ዓባይ እንተ ጸንአት ላዕሌነ ጥቀ በእተ ፈቃድነ እንተ ወጽአት እምሕላዌሃ እንተ ይእቲ ጥንተ ኃጢአት" (ቁር ፫፡፲፱)
- "እም ቀዲሙ ዘአበሰ ቦቱ አዳም፥ ወሶበ አበሰ አዳም ሶቤሃ ወለደ ዘከመ አምሳሊሁ" (አብሉዲስ ፴፪፡ ፱) ስለሚል የፒላጊዮስ አመለካከት በመላ ኦርቶዶክሶች የወደቀ ነው፡፡

ለዚህ ሐሳብ የተቀራረበ አመለካከት ከቅርብ ዘመን ወዲህ በአገራችንም ስለ ኦርቶዶክሱ ጥልቅ ግንዛቤ የሌላቸው ከሊቃውንቱ ጋር ያልዋሉ፥ ምሥጢር ያላደላደሉ ሜዳ አደግ ወገኖች ስለ እመቤታችን ሲናገሩ አዳም በበደለ ጊዜ "ዘርን ከፍሎ አስቀረለን" በማለት ከቅዱሳት መጻሕፍት የማይገኝ ልብ ወለድ ትምህርት ያስተምራሉ::

**ሐ.** ፒላጊዮስ የሚያምነው ክርስቶስ የሞተው ለሞራል ምሳሌነት ብቻ እንደሆነ ነው፥ ኦርቶዶክሳውያን ግን የክርስቶስ ሞት ይቅርና፥ የጻድቃን የሰማእታት ሞት እንኳ ቢሆን፤ የግላቸውን ሞት እንደሞቱ ብቻ ሳይሆን፥ ለሞራልም ለሃይማኖትም እንደሞቱ እናምናለን:: ጣሊያንን "እንኳን ሰው መሬቷ አትገዛልህ" እያሉ ስለ ሞቱት ስለ አቡነ ጴጥሮስ ሞት የዜግነትንና የሃይማኖትን ግዳጅ መወጣት እንደሆነ አባቶቻችን ነገሩውናል:: ስለዚህ ፒላጊዮስን በተሰደደ ጊዜ የተቀበሉት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እሱ የሚያምነውን እምነት ስለተቀበሉ ነው ማለት በባዛንታዮችና በኦሬንታልሎች ዘንድ ተቀባይነት የለውምና፥ አብቀወ አፉሁ!

**መ.** *"የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ለፒላጊዮስ መጠለያ ሰጥተዋለች፥ ይህም በትምህርቱ መስማማቷን ያሳያል"* ይላል:: ስደተኛን መቀበል ማለት የተሰደደውን ሰው ሃይማኖትና የግል ታሪክ መቀበል አለመሆኑን ከእኛ ከኢትዮጵያውያን የበለጠ ማንም ሊመሰክር አይችልም:: ለምሳሌ ተሰደው ወደኛ የመጡትን መሐመዳውያንን የተቀበሉ ኢትዮጵያውያን፥ የተቀበሉት ሰብአዊነትን እንጅ እምነታቸውን እንልነበረም:: እኛም ወደ ምዕራቡ ተሰደን ስንመጣ ምዕራባውያን ሃይማኖታችንን ተቀበሉ

ማለት አይደለም:: እንደዚሁ ሁሉ የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ለፒላጊዮስ መጠልያ የሰጠችው በሰባዊ ርኅራኄ ነበር:: እሱ ግን ወደ ሃይማኖት በማስጠጋት ለራሱ ማደናገሪያ እንደ ማስረጃ አቅርቦታል:: አብቀወ አፉሁ!

በተሰደደው ፒላጊዮስና በስደት ላይ የተሰነዘረውን ውሸት ከዚህ ላይ አቁሜ፥ *"መደምደሚያ የማደርገው በየዋሕነት አለዚያም ከወቅታዊ የሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ጋራ በማያያዝ ገብቷቸውም ሆነ ሳይገባቸው እሳቸውን ለሚከተሉ ምእመናን የምሰጠው ማሰሰቢያ ነው"* 208:: ብሎ በተነገረው አንቀጾች በገጽ 208 እስከ ገጽ 209 ላይ በአንቀጽ ከቁጥር፩ እስከ ቁጥር ፯ ወደዘረዘራቸው እሻገራለሁ::

እኔንም የከንሳስ መድኃኔ ዓለም ምእመናንንም ሳያውቀን፥ መከፋፈል በለመደ አንደበቱ *"ከወቅታዊ የሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ጋራ በማያያዝ ገብቷቸውም ሆነ ሳይገባቸው እሳቸውን ለሚከተሉ ምእመናን የምሰጠው ማሰሰቢያ"* እያለ ለመከፋፈል በሰነዘረው ሽፍጡ፥ ከፋፋይና ጸረ ሃይማኖት መሆኑን በራሱ አንደበት ገልጾታል:: <u>እኔን በተመለከተ፥ በሄድኩበት ቦታ ሁሉ፥ የተዋሕዶው ኦርቶዶክስ ነገረ መለኮት በሚመራን አቅጣጫ አብረን ክርስቶስን እንከተል ብየ ከማስተማር በቀር፥ እኔን ተከተሉኝ ብየ አስተምሬም፥ ተናግሬም አለውቅም:: እኛን ተከተሉን ብለው የሚአስተምሩትንም በጥብቅ የምቃወም ነኝ</u>:: <u>የከንሳስ መድኃኔ ዓለም ምእመናን የሚከተሉት እኔን ሳይሆን በኦርቶዶክሱ ነገረ መለኮት ግንዛቤ የተረዱትን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው</u>:: ይህ አባባሉ፥ <u>እሱና የሱ ቢጤዎች በኔም፥ በአንዳንድ አባቶች ላይም ጠልቶ ለማስጠላት ከሕዝቡ ለመለየት ያደረጉትን የሐሰትና የስም ማጥፋት ዘመቻ አሁንም እያካሄደ ነው</u>::

**ለምሳሌ:-**

፩ኛ ብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴን **'ጸረ ማርያም'** ናቸው ብሎ በሐሰት ለማስጠላት እነደ መ'ሞከሩና፥ ፪ኛ **"ክርስቶስ ሥጋን ፈጥሮ ተወሐደ፥ በሥጋው ፍጡር ነው"** ተብሎ በመጽሐፍ ተጽፎ የሚገኘውን በጉባዔ የተማርነውን እውነተኛ ሃይማኖት ትምህርት በማስተማራቸው ጠልተው ለማስጠላትና በምቀኝነት ከሕዝብ ለማራቅ በአባ መአዛ ላይ በጽሑፍ፡ ባሉባልታ እንዳሰራጩ ሁሉ፥ ዛሬም እኛን ለሃይማኖታችን ብለን ባንድነት የቆምነውን ለመከፋፈል የሰይጣን መፈክሩን ያስተገባል::

**ረ.** *"በእኛና በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚታመነው ማነኛውም ሕጻን ከእናቱና ከአባቱ ከሥጋቸው ሥጋ ከነፍሳቸው ነፍስ ነስቶ ይወለዳል"* ይላል:: ይህ አደናጋሪ ግለሰብ የኛንም ሆነ የሮማ ካቶሊክ ነገረ ሃይማኖትን ሳያውቅና ሳይረዳ ያልገባውን፥ ያልዋለበትን ነገረ መለኮት እያምታታና እየደበላለቀ ያቀርባል:: <u>እኛ ኦርቶዶክሶች **"ማነኛውም ሕጻን ከእናቱና ከአባቱ ከሥጋቸው ሥጋ ከነሳቸው ነፍስ ነስቶ ይወለዳል"**</u> ስንል፤ <u>የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ግን</u> "The Roman Catholic Church teaches that every spiritual soul is created immediately by God - it is not "produced" by the parents ... " ትላላች:: ማለትም፥ **"ጽንስ በተከናወነባት ቅጽበት እግዚአብሔር ነፍስ ይፈጥራል"** ማለት ነው:: እሱ እንዳቀረበው እኛ የምንለውን አይሉምና፥ **አብቀወ አፉሁ!**

# ፩ኛ፡- “ጥንተ አብሶ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አላገኛትም”

በጠልሰሚ ገጽ 208 ላይ *“ጥንተ አብሶ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አላገኛትም” የሚለው የነገረ ማርያም ይትበሐል አስተርአየ ጸጌ እንደሚፈርጁት ዘመን አመጣሽ ሳይሆን ጥንታዊ መሆኑን መገንዘብ አለባቸው”* በማለት በስማ-በለው ሊነግረን ሞክሯል:: ይህ ትምህርት እንኳን ለእኛና ለመላ ኦርቶዶክሶች ቀርቶ፥ ለራሷ ለሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም ከጊዜ በኋላ የመጣ እንግዳ እንደሆነና ጥንታዊነት እንደሌለው፥ በ December 8, 1854 Pope Pius IX እንዳወጀውና ሊቃውንቱ እንዳልተቀበሉት በታሪክ የተመዘገበ ነው:: የቀሩት አብያተ ክርስቲያናት ጥንት የሌለውን አዲስ ትምህርት አስገብተሻል ብለው የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ከሸሹባቸው ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ መላው ዓለም ያውቀዋል:: ይህ ትምህርት አዲስ ለመሆኑም፡- በዲሲ ዙሪያ የተቋቋመው የማኅበረ ካህናቱ ጉባዔም በደረሰበት በ፲፱፺፯ ዓ.ም. ጥናት *“ከጊዜ በኋላ የመጣውና ሕዝበ ክርስቲያኑን በመከፋፈል ላይ ላለው እንግዳ ትምህርት ቅድሚያ በመስጠት ችግሩ በየቦታው እየተዛመተ በቤተ ክርስቲያናችን መለያየትን እያስፋፋ እንዳይቀጥል:: በተለይም እስከ ዛሬ ወልድ ዋሕድ በማለት አንድ ሆነን ከኖርነው ከአራቱ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋራ ያለንን የነገረ ሃይማኖት አንድነት እንዳያስቀርብን ብሎም እንዳይለያየን.... እናት ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምሮ ስትጠቀምበት የነበሩትን ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቀድሞ ሊቃውንትን እምነት ባገናዘበ ሁኔታ የማያዳግም ውሳኔ ይስጥበት”* በማለት ለቅዱስ ሲኖዶስ የላከው ማስረጃ ያረጋግጣል፡፡ እሱም ራሱ ይህ ትምህርት

አዲስ ለመሆኑ፥-

- *“ከከልቄዶን ጉባዔ በፊት ጀምራ አኀት አብያተ ክርስቲያናትን ሳታማክር ብዙ የሃይማኖትና የቀኖና ውሳኔዎችን በግሏ ስትወስን በመኖሯ በሌሎች ዘንድ ብዙ ቅሬታን ፈጥራለች”* (91) በማለቱ
- *“በዘመናዎቹ ውስጥ ካቶሊካዊ ነገረ ማርያም እየናረ ሄዶ ወደ አምልኮ ማርያም (Mariolatry) እንደተጠጋ በሰፊው የታወቀ ነው”*(106):: በማለቱ
- *“አመች የመሰላቸውን ጊዜ ጠብቀው አዲስ ሕገ ሃይማኖት እንዲወጣ መጠየቅና የአብያተ ክርስቲያናትን አንድነት የሚያውክ ነገር መፍጠር”* (107) :: በማለቱ
- “ካቶሊኮች ማንንም ሳያወያዩ በተናጠል ማርያማዊ ነገረ ሃይማኖት በዶግማ ደረጃ አከታትለው አውጀዋል(171 እና 177):: በማለቱ
- ፈረንሳይ ውስጥ በርናዴት ለተባለች ገጠሬ ልጃገረድ ድንግል ማርያም በራዕይ ተገልጣ (in 1858. At Lourdes a 14-year-old girl, Bernadette Soubirous, claimed that a beautiful woman appeared to her and said, *‘I am the Immaculate Conception’*).’ እኔ ያለኃጢአት የተጸነስኩ

ነኝ" ብላ ድንግል ማርያም ነገረችኝ ብላ ያወራችውን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሰሙ ጊዜ በ1958 አስደናቂ ራዕይ ብለው ማርያማዊ ሕገ-ሃይማኖቱን ለማጽደቅ ሆን ብላ እንደተገለጠች ቆጥረውታል:: (82-3) በማለቱ፥

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን *"አሁን በነገረ ማርያም ከእነሱ ብትለይ የሚያስፈራት ወይም የሚቀንስባት ምን ሊኖር ይችላል?"* በማለቱ፡ ይህ ትምህርት ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ያልነበረ መሆኑንና፥ አዲስ የመጣ መሆኑን በራሱ አንደበት አረጋግጧል::

# ፪ኛ "ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት" በሊቃውንት ጉባዔ ተመርምሮ የጸድቀ ማስመሰል

በዚሁ አንቀጽ ላይ *"ዶግማው በኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባዔ ተመርምሮና ጸድቆ በጽሑፍ የታወጀ ሕገ ሃይማኖት መሆኑን ማወቅ አለባቸው"* ይላል፡፡ እሱ የሌለውን ፈጥሮ ማውራት ልማዱ ስለሆነ የሌለውን ነገር ይቀባጥራል እንጅ፥ እስካሁን ድረስ ስለ እመቤታችን በሚደረገው ጥናት የተጻፉት ሁሉ ነገረ ማርያም በሚል እንጅ በኛም ሆነ በመላ ኦርቶዶክሶች *"ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት"* ተብሎ የታወጀም ሆነ ተጽፎ የሚገኝ መረጃ የለም፡፡ መታወጅ ቀርቶ ሊታሰብና ሊነገር ፈጽሞ የማይገባ ነው:: "ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት" ብሎ ራሱ ለፈጠረው ፈጠራ ማስረጃ አድርጎ ያቀረበው መጽሐፍ፥ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ያላገኘ ነው:: እሱ ራሱም *"ቀኖናዊነት ባያገኝና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቁጥር ውስጥ ባይገባም"* በማለቱ አረጋግጧል:: ስለእመቤታችን ድንግልና እና ቅድስና ምንጮች የሆኑት መጻሕፍት፥ ነቢዩ ዳዊት *"መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን"* እንዳለው፥ ብሉያትና ሐዲሳት ናቸው:: እሱ የሃይማኖት መሠረት ስለሌለው፥ የእመቤታችንን ቅድስናና ድንግልና በቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የሌለውን መጽሐፍ መሠረት አደረገው:: አብቀወ አፉሁ!

*"ጥንተ አብሶ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አላገኛትም"* የሚለው እመቤታችን ሙሉ ሰው ሆና ወደዚህ ዓለም አልመጣችም ወደሚል የተሳሳተ አቅጣጫ ስለሚወስድ መቀበል ቀርቶ፥ እኛ ኦርቶዶክሶች አጠንክረን የምንቃወመው ነው:: ይልቁንም አላዊ (ከሐዲ) ንጉሥ፥ መናፍቅ(ተጠራጣሪ) ጳጳስ ይነሳል፥ ያን ጊዜ በጉባዔ የተማራችሁትን አትልቀቁ እያሉ ያስተማሩንን ሊቃውንት አበው እንደነ ደፍተራ ገለፈት ልንጠራጠራቸው አይገባም:: ከሊቃውንት አበው የተረከብነውንም እነደፍተራ ገለፈት በሚፈጥሩት ግርግር የምለቀው አይደለም:: አጻደቀው የሚለውንም ሲኖዶስ ይህን በመወሰኑ ተሳቷል::

ብለን ልንቀበለው ቀርቶ ሐላፊነቱን የዘነጋ ቅዱስ ሊባል አይገባውም እላለሁ:: ይህንም ስል፥ "ወክርስቶስ እግዚእነ ወአምላክነ ይዕቀባ ዲበ ዛቲ ኮኩሕ ለዛቲ ሃይማኖት ርትዕት ዘእንበለ ሕልፈት እስከ ፍጻሜ ለዛቲ ዓለም ከመ ተሀሉ እንዘ ትገብር ባቲ በቃለ ጽድቅ ዘከመ ቀኖናሃ ለቤተ ክርስቲያን ወምክረ ተአማንያን በንባብ ርትዕት እንተ ኢኮነት ርስሐተ"(፲፭፥፲፯) ማለትም፥- "በጴጥሮሳዊት ሃይማኖት ላይ የተመሠረተችው ቀጥ ያለችው ኦርቶዶክሳዊት እምነት ሳትለወጥ ሲነገርባት እስከ ዓለም ፍጻሜ ጸንታ እንድትኖር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ይጠብቃት" በሚል የተናገሩትን ተመርኩዤ ነው፡፡

ይልቁንም አቡነ ጳውሎስና የሚመሩት ሲኖዶስ፥ አቡነ መልከ ጼዴቅን ከጎብረተ ሰቡ ጉያ ለማስወጣት በፈጠሩት አዲስ የጥንተ አብሶ ዶግማ በብዙ መንገዶች የሚጠየቁበት ከፍተኛ ኃጢአት ነው:: በአቡነ መልከ ጼዴቅ እግር ላይ ወድቀው ይቅርታ በመጠየቅ፥ አቡነ መልከ ጼዴቅ ይቅር ካላሏቸው በቀር፥ በእግዚአብሔርና በመላ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ፊት፥ እንዲሁም ይህን በተመለከተ የተሰነዘረባቸውን ውግዘት እያነበበና እየተገነዘበ በመጣው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ፊት ከባድ ሐፍረትና ሊወጡት ከማይይችሉት አዘቅት ውስጥ መውደቃቸው ከዚህ በታች የዘረዘርኳቸው አርስተ ነገሮች ይጠቁሙናል::

# በአቡነ ጳውሎስና በሚመሩት ሲኖዶስ በ'ጥንተ አብሶ ዶግማ' ስም የፈጸሟቸው በደሎች:-

**ሀ.** አቡነ ጳውሎስ እመቤታችን ያለ ጥንተ አብሶ አልተወለደችም ብለው ራሳቸው በእንግሊዘኛ የጻፉትን የኢትዮጵያ ሕዝብ አይደርስበትም በማለት በ Princeton Theological Seminary ቤተ መጻሕፍት ደብቀው፥ ከጊዜ በኋላ መሠረተ ቤተ ክርስቲያንን ለማናጋት ከሞከሩ ሰዎች ጋራ በማበር የሚጠሉትን መጉጃ የሚከተላቸውን መጥቀሚያ በማድረግ ነገረ መለኮቱን ለፖለቲካ ተጠቅመውበታል ከዚህ የበለጠ ሽፍጠኛነት ምን አለን?

**ለ.** ብጹዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ "በእመቤታችን ላይ ጥንተ አብሶ ነበረባት ብለዋል" ተብሎ የተሰነዘረባቸው ውግዘት በሕዝብ ተጠልተው ብቻቸውን እንዲቆሙ ለማድረግ የተደረገ ደባ እንጅ ተገቢ ውግዘት እንዳልሆነ ያውቃሉ:: አቡነ መልከ ጼዴቅ አላሉም እንጅ ቢሉም ይህ ትምህርት፥ ከሳቸው በፊት የነበሩት የሃይማኖት አባቶቻቸው የኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት አበው ትምህርትና እምነት ስለሆነ ማስወገዝ ቀርቶ የሚያስጠይቃቸው አልነበረም:: ሆኖም አቡነ ጳውሎስ በተሰነዘረው የተሳሳተ ውግዘት ተባብረዋል:: ወጣቶችንም እየላኩ እንዲዘምቱባቸው አድርገዋል:: ይህንስ ቢሆን እንኳን መነኩሴ፥ ዶክተር፥ ሽማግሌ፥ ፓትርያርክ ነኝ የሚል ሜዳ (ስድ) አደግ ነው የሚባል ያደርገዋልን?

**ሐ.** አቡነ መልከ ጼዲቅ "እመቤታችን የለ ጥንተ አብሶ አልተወለደችም" ማለታቸው የሚያስወግዛቸው ከሆነ፥ አቡነ ጳውሎስ እመቤታችን ጥንተ አብሶ ነበረባት ብለው ጽፈው ፓትርያርክ ተብለው ለምን ተቀመጡ? በኛ ላይ የዘመቱ ሁሉ፥ የተፈጠረውን ግርግር በመጠቀም ጥቅም ለማግኘት እንጂ፤ ለሃይማኖቱ፥ ለቤተ ክርስቲያንና ለታሪክ ተቆርቁረው አይደለም:: አቡነ ጳውሎስ ላይ ከተነሱ

የሚከተላቸውን ርግጫና ጡቻ ስለሚያውቁ እንጅ፥ አቡነ ጳውሎስ ይህን እንደጻፉና እንደሚያምኑ ደጋግመን ስለጻፍን ሳይደርሱበት ቀርተው አይደለም:: ታዲያ እነዚህስ ቢሆን አቡነ ጳውሎስን አቅፈው ቅዱስ እያሉ፥ ሌላውን ንቀውና አቃለው ማቅረብ የክርስቲያን ተግባር ነው ሊሉ ነውን?

*መ.* አቡነ መልከ ጼዴቅ አሉ ተብሎ ስለተወገዙበት ጥንተ አብሶ፥ ነፍሳቸውን ይማርና *መጋቤ ብሉይ ሰይፈ "አንዳንዶች እመቤታችን አድፎ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ:: ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶድክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም:: ምክንያቱም እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት እንጅ ከሰማይ የወረደች የመላእክት ወገን አይደለችምና:: ካሳ የማያስፈልጋትም ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው ካሳ ከተከፈለላቸው ወገን ናት:: ሆኖም እንደ አዳምና ሔዋን የምኞት የመናገርና የገቢር ኃጢአት ፈጽሞ የለባትም"* ብለው አረጋግጠው የመሰከሩ ሊቅ፥ ከዚህ ዓለም በሞት እስኪለዩን ድረስ የሊቃውንት ጉባዔ ሰብሳቢ ነበሩ:: ይህ የሚያስወግዝ ከሆነ፥ መጋቤ ብሉይ ሰይፈን የሊቃውንት ጉባዔ አርጎ፥ ስለዚህ ጉዳይ ምንም ባላሉና ባልጻፉ አቡነ መልከ ጼዴቅ ላይ የውግዘት ሸከም መጫን የግፍ ግፍ አይደለምን? ከዚህ የበለጠ ምን ኃጢአት አለ? በጎሰኝነት፥ በመንደርተኝነት፥ በፖለቲካና በግል ጥላቻ ሕሊናው የጨለመበት ሰው ካልሆነ በቀር፥ ከ *ሀ* እስከ *መ* በዘረዘርኳቸው ተግባሮች አቡነ መልከ ጼዴቅንና አቡነ ጳውሎስን በፍርድ ሚዛን እንዴት እኩል መመዘን ይቻላል?

ከ *ሀ* እስከ *መ* የዘረዘርኳቸው በደሎች ውሸቶች አይደሉም:: ታዲያ የቤታችን መመሪያ "ወለእመሰ ውእቱ አሥረ ወአውገዘ ዘእንበለ ርትዕ እንዘ የሐሥሥ ከመ ያተክዞሙ ለሰብእ ወይፈቅድ ስሕተቶሙ ወተጋንዮቶሙ ሎቱ ይኩን ውእቱ እሡረ ወውጉዘ እምኀበ እግዚአብሔር:: ወይቁሙ ለዕሴሁ ካህናቲሁ በጽድቅ ዘይደሉ"(ፍ.ነ. አ ፭ ቁጥ ፻፹፩) ማለትም፡-*"ሰውን ጎድቶ ለማሳዘን ሲል፥ ወይም ሰዎች ያወግዞናል ብለው በመፍራት እንዲታዘዙት በማይገባ ቢአወግዝ፥ እርሱ ራሱ በእግዚአብሔር ዘንድ የታሠረ የተወገዘ ይሁን:: ካህናቱም በማይገባ ያወገዘውን እንደቀላል ነገር ታዝበው አይልቀቁት"* ይላል:: ያለበቂ ምክያት ያወገዘውን ጳጳሳቱ ተስማምተው ቢተውት እንኳ ካህናቱ እንዳይለቁት የተሰጠ ጥብቅ መመሪያ ነው:: አቡነ ጳውሎስን ለመርዳት ስንል ቀደን ካልጣልነው በቀር፥ ይህ ጥብቅ መመሪያ እንዴት ሊታለፍ ነው? ደፍተር ገለፈት በገጽ 108 ላይ *"ወልዳ ያሳደገችውን እናት ገበና ለመግለጥና ዓይኗን ለመጓጎጥ የሚደፍሩና የሚጨክኑ መናፍቃን የተሐድሶ ጎራዎች ናቸው"* እያለ ለማይረባ ጥቅም ሲል የፈጠረው መዘዝ፥ የጎረጥ እያየን ያለፍነውን ያቡነ ጳውሎስን ገበና እንድንገልጸው አስገደደን::

ይህን የቤተ ክርስቲያናችንን መመሪያ ያልተረዳ ደፍተራ ገለፈት፥ በአቡነ ጳውሎስ የሚመራውን ሲኖዶስ የፈጸመውን ትልቅ ስሕተት ደብቆ፥ የቤተ ክርስቲያናችንን እምነትና ታሪክ ለማፍረስ በቅዱሳን አባቶቻችን ላይና በቅዱሳት መጻሕፍቶቻችን ላይ የዘመተ መሆኑን እሱ ራሱ *"አስቀድሜ ማስረገጥ የምፈልገው"* እያለ፥ በድፍረትና በትዕቢት የተናገረውን እጠቅሳለሁ:: *"አስቀድሜ ማስረገጥ የምፈልገው ሊቃውንተ-ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖት አባቶቻችን ናቸው ብለን የምንቀበላቸው በጻፉትና በተናገሩት ሁሉ ፍጹማን ናቸው ብለን አይደለም፡፡ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚታወቀው፥ ከአንጋፋዎቹ ብዙዎቹ፥ በአስተሳሰባቸው አንዳንድ ሕጸጽ ይታይባቸዋል:: ስለዚህ እነሱ የሚያቀርቡት የግል ሐሳብና ትርጓሜ ያለ*

*አንዳች ጥያቄ በጭፍን መቀበል አንችልም :: አይገባንምም :: ለምሳሌ ቀጸዶቃውያን አባቶች ባስልዮስ ጎሮጎርዮስ ዘእንዛዙ፥ጎርጎርዮስ ዘሰኑይ በትርጓሜያቸው እመቤታችን ጥንተ አብሶ እንዳለባት የሚያመለክት አዝማሚያ ማሳየታቸው አይካድም"* (187) በማለቱ ከውጭ የቀላወጠውን የተሳሳተ እምነቱንና ትምህርቱን በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ለመትከል፥ የጥንቱንና እስካሁን የነበረውን ኦርቶዶክሱን ነገረ መለኮት ነቃቅሎ ለመጣል ሞክሯል:: ይሁን እንጅ ሳያምንበት ለሚያገኛት ሳንቲም ሲል ብቻ፥ *"መቀበል አንችልም አይገባንም"* የሚላቸውን ሊቃውንትና ያዘጋጇቸውን መጻሕፍት ቅዳሴ በመጠቀም መቀደሱ፥ አብረውት ለሚቀድሱ ለነ ዶክተር አማረና ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ትልቅ ሐፍረት አይደለምን? የእነዚህን ሊቃውንትና የመጻሕፍቶቻቸውን ክብርና ቅድስና በመላ ኦርቶድክስ አብያተ ክርስቲያናት መቃወም ቀርቶ የሚጠራጠር የለም:: ያስተማሩት ትምህርት "እስመ ለሃይማኖትነ ርትዕት እንተ ነሣዕናሃ ወተምህርናሃ እም አበዊነ ሐዋርያት፡ ወአርትዕዋ አበው፥ ወከሰትዋ እመጽሐፈ ብሉይ ወሐዲስ ወእምነብያት"(ሃ.ምዕ ፻፺፡፲፩) እንዲል፥ ማለትም፡- ከአባቶቻችን ሐዋርያት የተማርናት የእነሱ ተከታዮችም ከኦሪት፥ ከነብያትና ከሐዲሳት ሳይወጡ አፍታተው ያስተማሯትን እስከዓለም ፍጻሜ እነከተላለን እያሉ እንጅ፥ አሁን በዓለም ፍጻሜ እራሱ ከቁጥር አልገባም የሚለውን የያዕቆብን ወንጌል የሚቃወሙ ናቸው::

# እመቤታችን ከሰው የተለየችው ከሐናና እያቄም 'ያለጥንተ አብሶ' ተጸንሳ በመወለዷ አይደለም

"ወኩላ ብእሲት ዘትትዌከፍ ዘርዐ ወትወልድ ተባዕተ ትከውን ርኩስተ:: ወባሕቱ ልደቱሰ ለክርስቶስ በሥጋ ኮነ እመንፈስ ቅዱስ ወቅድስት ማርያም ድንግል በመንክር ግብር ወበአምሳል ዘኢይትነገር ባቲ፡ ወዓዲ ይቤ ውእቱሰ ኮነ ምእመነ በኀበ ዘፈነዎ" (ሃ.አ. ምዕ ፻፳፬፡ ቁጥ ፴፩):: የጌታችን የክርስቶስ ከእመቤታን በመንፈስ ቅዱስ የተወለደው ሥጋዊ ልደት ባንደበት ሊገለጽ የማይቻል አስደናቂ ነው:: በወር አበባና የወንድ ዘር ተቀብላ ከምትወልድ ሴት የተለየ ነው:: ሐና እመቤታችንን የወለደቻት የወር አበባ አይታ፥ ከኢያቄም ዘር ተቀብላ እንጅ በገብረ መንፈስ ቅዱስ አይደለም::

ኤራቅሊስ የተባለው አባት፥ የጌታችንን ጽንስ ከተራ ጽንስ ለመለየት የሌላዋን ሴት አጸናነስ "ርኩስት" ይላል:: "ርኩስት" የምትለዋን ቃል ካነሳሁ ዘንድ ያደኩበት አካባቢ ያስገድደኛልና፥ ለደፍተራ ገለፈት አንዷት ጠባብ የወንድ በር እሰጠዋለሁ:: "ወዮሴፍሰ ፈሐሪሃ እስመ ጻድቅ ውእቱ ኢፈቀደ ይክስታ ወመከረ ጽሚተ ይህድጋ"(ማቴ ፩፡፲፱) ማለትም "ዮሴፍ ጻድቅ ነበረና፥ ሊአጋልጣት አልፈለገም፥ በጥሞና ሊተዋት ወሰነ" ብሎ ጭምትነቱን ቢገልጥም፤ መልአኩ በሕልሙ የማበረታቻ ቃል የተናገረውን ለማብራራት ኤራቅሊስ የተባለው ሊቅ "መልአ ከርሳ ለድንግል ወተሐውከ ልቡ ለዮሴፍ ሶበ ርእየ ልሕቀተ ከርሣ ለእንተ እንበለ ርኩስ ሐለየ ፍጹመ ምሥጢራ ለንጽሕት ወረከበ ጽንስተ በምሥጢር ዘኢየአምሮ ወወድቀ ውስተ ጽኑዕ መዋግደ ሕሊና እንዘ ጽንስት ወነጻራ እንዘ ጽንስት ወሐለየ ከመ ይእቲ ኮነት ውስተ ርኩስ እስከ አመ አስተርአዮ መልአከ እግዚአብሔር ወይቤሎ ኢትፍራህ ኦዮሴፍ እስመ

ዘይትወለድ እምኔሃ እመንፈስ ቅዱስ ውእቱ ወአኮ በከመ ትትሔዘብ አንተ” (፵፰፡ ፴፩) በማለቱ አንድ ጎረምሳ አስነውሯታል በማለት መረን ከለቀቀ አነጋገሩ በቀር፥ ዮሴፍ በዘር የጻነሰች መስሎት መጨነቁ ልክ ነው:: ይሁን እንጅ እመቤታችን ከእርሷ በፊትና ከእርሷ በኋላ ካሉት ሴቶች የተለየችው ከዚህ በታች በሰፈሩት ምስክሮች እንጅ ያለጥንተ አብሶ ተጸንሳ በመወለዷ አይደለም::

ሀ. ገብርኤል “አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ” (ሉቃስ ፩፡፳፰)

ለ. እራሷ እመቤታችን “ወንድ ሳላውቅ እንዴት ይሆናል” (፩፡ ፴፬)

ሐ. ኤልሳቤጥ “አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ” (ሉቃ ፩፡ ፵፪)

ከሶስቱም የመነጨትን ምስክሮች አባቶች የሚተረጉሙት “ልማደ አንስት” ማለትም ሴቶች ጸንሶ ለመወለድ ከሚያስፈልጋቸው የተፈጥሮ ሕግ ውጭ በመሆኗ ገብርኤልም ኤልሳቤጥም “ከሴቶች የተለየሽ ነሽ” እያሉ ተናገሩ እንጅ ከሰው የተለየሽ ነሽ አላሉም:: “ተወሐደ በጊዜ አብሠራ ሊቀ መላእክት ወሐራ ሰማያውያን ገብርኤል ዘተአመነ ላዕለ ዝንቱ ምሥጢር ኅቡዕ ወሥርአት አምላካዊ ዘኢይትነገር ወአብሠራ ተፈስሂ ፍስሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምሥሌኪ” (ሃ አ. ምዕ ፺፡፲፩) እንዲል፥ ገብርኤል እስኪ አበሥራት ድረስ የምታውቀው ነገር አልነበረም:: የገብርኤል ብሥራት ከያዛቸው ምሥጢራት አንዱ ለእሷ መግለጽ ነበር:: “ወንድ ሳላውቅ” ማለቷም፥ ከሰው ውጭ አለመሆኗን በማወቋና፥ ከሴቶች ልማድ የራቀችና ለጌታ እናትነት መመረጧን ባለማወቋ ነበር::

“ማርያምኒ እመ ስዕነት አእምሮ ማርያም ምሥጢር፥ (ለዓለም)

ምሥጢረ ማርያም ለማርያም ገብርኤል ይነግር፥

እመኒ ሐለፈ ዘመነ ሥጋዌ ማእረር፥

ዘርዐ ተራድኦ ከመ ይዝራዕ ኅበ ቂርቆስ የሐውር” እያሉ

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት እነ አለቃ ተክለ ጽዮን አስተምረውናል:: በዚህ መሠረት *“የጥንተ አብሶ ጉዳይ ድንግል ማርያም ከእኛ ጋር አንድ ከሆነችበት ሰብአዊ ተፈጥሮ ጋር ሳይሆን ከእኛ ከምትለይበት ቅድስናዋ ጋራ ተዛምዶ መታየት ይገባዋል”* 192 ይላል:: እመቤታችን ከኛ የምትለየው ያለጥንተ አብሶ በመወለዷ ሳይሆን፥ ጌታችንን ከመውለዷ በፊትም ሆነ ከወለደችው በኋላ በራሷ የፈጸመችው የሀልዮ፥ የነቢብና የገቢር ኃጢአትና በደል ያልተገኘባት በመሆኗ፥ በእግዚአብሔር በመመረጧ፥ በድንግልና ጸንሳ በድንግልና በመውለዷ፥ የአምላክ እናት በመሆኗ ነው:: ይሁን እንጅ እመቤታችን ከጥንተ አብሶ የነጻቸው በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት ጊዜ ለመሆኑ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችንም ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን አባቶች ሲነገር የመጣውን መሠረት በማድረግ ከዚህ የሚከተለውን እየመሰከሩ አልፈዋል::

# የኢትዮጵያውያን ሊቃውንት አባቶች ምስክርነት፡-

፩ኛ መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ "መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሆ ማለትም ትስብእትን ከአዳም መርገም አንጽቶ ቀድሶ ለተዋሕዶ መለኮት የበቃ አደረገው" (መድ ገጽ ፲፯-፳፩)

፪ኛ አለቃ አያሌውም ታምሩ "መላኩ ገብርኤል በአበሰራት ጊዜ ሥጋዋም ነፍሷም በመንፈስ ቅዱስ ተቀደሰ፥ አዲስ ሕይወት አገኘ... የመጀመሪያውን ቅድስና ከሰው ልጆች ሁሉ በፊት ለእግአብሔር እናት በመሆኗ ታደለች:: በዚህም መሠረት 'ሰውነቴ በአምላኬ በመድኃኒቴ ደስ ይላታል' ብላ ለመናገር በቃች" (ወላዲተ አምለክ በኢትዮጵያ ገጽ ፳፰ ፥፲፱፻፶፱ ዓ.ም.)

፫ኛ ነፍሳቸውን ይማርና መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ዮሐንስ፥ ለረዥም አመታት፥ በቅኔ መምሕርነት፥ ከዚያም በየጉባዔዎች በመገኘትና በቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ቤት በመደበባኛ አስተማሪነት ሲአገለግሉ ከቆዩ በኋላ፥ ይህችን ዓለም በሞት እስከለቀቁባት ሰዓት ድረስ የሊቃውንት ጉባዔን በሊቀመንበነት በማገልገል ላይ የነበሩ ከሊቃውንት አባቶቻችን አንዱ የዘመናችን ሊቅ እንደነበሩ የታወቀ ነው:: እሳቸውም "የኢትዮጵያ ኦርቶድክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት እና የካህናት ተልእኮ" በሚል ርዕስ መጽሐፍ አዘጋጅተዋል:: ይህንኑ ያዘጋጁትን መጽሐፍ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መመሪያ በትምህርተ አበ ነፍስ አገልጎት ክፍል፥ ሰኔ ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ.ም.አሳትሞታል:: በዚህ መጽሐፍ ገጽ ፳፱ ላይ "አንዳንዶች እመቤታችን አድፎ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ:: ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶድክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም:: ምክንያቱም እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት እንጅ ከሰማይ የወረደች የመላእክት ወገን አይደለችምና:: ካሳ የማያስፈልጋትም ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው ካሳ ከተከፈለላቸው ወገን ናት:: ሆኖም እንደ አዳምና ሔዋን የምኞት የመናገርና የገቢር ኃጢአት ፈጽሞ የለባትም" ብለው የኦርቶዶክሱን ትምህርትና እምነት በሚገባ ገልጸውታል::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተፈጠሩት የኦርቶዶክሱን ትምህርትና እምነት ተቃዋሚወች እነ ደፍተራ ገከፈት፥ ሳይቀሩ "አንጺሆ ሥጋሃ ቀዲሶ ኪያሃ ሐደረ ላዕሌሃ" እያሉ እስከ ዛሬ ድረስ በዜማ ከመጮኽ በስተቀር ትርጉሙን ሳያውቁት ሲዘምሩት እንደቆዩ የታወቀ ነው:: ካለፈው እሁድ በፊት እመቤታችን ወደ ቤተ መቅደስ የገባችበትን በዓል ምክንያት በማድረግ፥ በከበሮና በጸናጽል ይህንኑ ቃል በመደጋገም ሲያዜሙ የሰሙ ምእመናን "ከበሮ ከመደብደብና ከመረግረግ በቀር የነገረ መለኮት ግንዛቤ የሌላቸው የሚዘምሩትን እንኳ ያልተረዱ ናቸው" በማለት የሰሞኑ መነጋገሪያ አድርገውታል::

ደፍተራ ገለፈት "አንጺሆ ሥጋሃ ቀዲሶ ኪያሃ ሐደረ ላዕሌሃ" የሚለውን *"አስተርአየ ጽጌ እንደሚፈርጁት ዘመን አመጣሽ ሳይሆን ጥንታዊ መሆኑን መገንዘብ አለባቸው"* ብሏል:: ይህ ትምህርት ለኛ ቤተ ክርስቲያን ባእድና አዲስ ለመሆኑ አሁንም በሕይወት ያሉ እውነተኞች ሊቃውንትና ከነ ቅዱስ ባስልዮስና ጎርጎርዮስ ጀምሮ እስከነ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ ድረስ የነበሩት የቤተ

ክርስቲያናችን አባቶች የመሰከሩት ነው:: እኔም ካባቴ ማሳ ቀጥፌ፥ ከናቴ መሶብና ድስት ጨልፌ ያመጣሁት ሳይሆን፥ ደፍሬ እንዳስተምረው ከነሱ የተማርኩት ስለሆነ "ጥንተ አብሶ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አላገኛትም" ብየ አላስተምርም:: ያለዚህ ተወለደች ማለት የሮማ ካቶሊኮችን መቀበል ነው:: "ጥንተ አብሶ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አላገኛትም" የሚለው መሠረት የሌላቸውና ከእኛ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ጋራ ዝምድና የሌላቸው ከ፲፱፹፬ ጀምሮ እንደነ ደፍተራ ገለፈት ያሉት ወራሪዎች በቤተ ክርስቲያናችን የዘሩብን የሰይጣን መፈክር ነው::

# ፫ኛ. ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ. ነጻ ስለሆነች ነገረ መለኮት ከኦሬንታል አቻወቿ የማትጋራ ማስመስል

"ቤተ ክርስቲያን የራሷ ቅዱስ ሲኖዶስ ያላት ነጻ ቤተ ክርስቲያን እንደ መሆኗ በሃይማኖትም ሆነ በሌላ ረገድ የኮፕቲክ ቤተ-ክርስቲያን ታዛዥ እንዳይደለች ማስታወስ ይገባቸዋል" በማለት እኛ ቤተ ክርስቲያናችንን የግብጽ ተገዥ ለማድረግ እንደፈለግን ለማሳየት ሞክሯል:: ቤተ ክርስቲያናችን የራሷ ቅዱስ ሲኖዶስ ያላት ነጻ ቤተ ክርስቲያን" መሆኗን ከእርሱ በፊት አውቀን ነፍሳቸውን ይማረውና በአቡነ ይስሐቅ ምክር ጉዳዩ በመጀመሪያ እዚሁ አሜሪካ ተቋቁሞ በነበረው ማኅበረ ካህናት እንዲታይ በመወሰኑ፥ በዲሲ ካህናት እንዲታይ ተደረገ:: ጉባዔው ያቡነ ማትያስን መሳሳት ተረድቶ፥ አቡነ ማትያስ የሰነዘሩት እገዳ ከመጽሐፍ ውጭና ችግር እንደሚፈጥር ገልጾ፥ በስሕተት አግኝለሁ ብለው የነገሩት የከንሳስ ሕዝብ እንዳይታወክ እገዳቸውን እንዲያነሱ፡-

- ሀ. አቡነ ገብርኤልን
- ለ. ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህን
- ሐ. መጋቤ አዕላፍ መክብብን ወደ አቡነ ማትያስ ላከ::

አቡነ ማትያስ "ቀሲስ አስተርአየ ተሳስቻለሁ ይበል" በማለት እገዳውን አላናሳም አሉ:: በሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ይመራ የነበረው ሶስቱን ያካተተ የካህናቱ ጉባዔ መልእክተኛም፥ "የተሳሳቱማ እርስዎ ነዎ" ቢላቸውም፥ አቡነ ማትያስ ቅዱሳት መጻሕፍትን የመረዳት አቅማቸው ዝቅተኛ በመሆኑ፥ ከቅዱሳት መጻሕፍት ይልቅ በቅርቡ ስሕተት ተሸክሞ በወጣው መመሪያ ራሳቸውን ጠቅልለው ወደቁ:: የማኅበረ ካህናቱ ጉባዔም "ወይቁሙ ለዕሌሁ ካህናቲሁ በጽድቅ ዘይደሉ" (ፍ ነ. አ ፳ ቁጥ ፻፹፩) በሚለው መመሪያችን መሠረት፥ ያቡነ ማትያስን እገዳ ሲመዘኑ ቀለው የተገኙበት ሆኖ አገኘውና አሽቀንጥሮ ጣለው:: አቡነ ማትያስ አግኝለሁ ያሉበት ትምህርትና እምነት የሮማ ካቶሊክ ሆኖ በመገኘቱ በአቡነ ማትያስ የሚደገፈው እንዲታረም ጉባዔው የወሰነውንና ያመነበትን በሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ፊርማ ለአቡነ ጳውሎስ ላከ:: መልሱን በጉጉት በመጠበቅ ላይ ሳለን፥ "ወይቁሙ ለዕሌሁ ካህናቲሁ በጽድቅ ዘይደሉ" የሚለውን መመሪያችንን አቡነ ማትያስና ተከታዮቻቸው ስለማያውቁት "ጳጳስ የወሰነውን

ካህናት ምን ሥልጣን አላቸውና እገዳውን ያነሳሉ” እያሉ ለእገዳው የተቃውሞ አጻፋ ማሰራጨት ጀመሩ:: በዚህም ሕገ ወጥ አካሄዳቸው ጵጵስናውን ከመመሪያ በላይ በማድረግ ወደ ከልትነት ለወጡት::

አቡነ ጳውሎስ በሐሰት የዘመቱባቸውን አቡነ መልከ ጼዴቅን ይቅርታ ጠይቀው በማረምና በማስተካከል ፋንታ፥ ባንድ ካህን ላይ ማርያምን ካደ ተብሎ በሰፊው ከተነገረበት ሕዝቡ ይሸሸዋል፥ የሚናገረውንም አይሰማውም፥ ይልቁንም በመተባበር ያወግዘዋል፥ በሚል ደካማ አስተሳሰብ እየተመሩ፥ በሐሰት የሚያሰራጩት ሁሉ ፕሮፓጋንዳ ክብደት እንዲያገኝ ከግብጽ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጋር የሃይማኖት አንድነታቸውን አወጁ:: “የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዝዳንት በሚል ለፈፋም ዓለምን ሁሉ እንደተቆጣጠሩ አድርገው በሚያሰራጩት ለፈፋ የሰውን ጆሮ ለመያዝ ሞከሩ::

ለነገረ መለኮቱ መዛባት፥ ለቤተ ክርስስቲያናችን ታሪክም መደምሰስ ምንም ስሜት ሳይኖራቸው ለፖለቲካቸው ሽፋን ሲሉ፥ ከግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጋራ ያንድነት ውል መፈራረማቸውን (Read the Protocol on http://www.medhanialemeotcks.org/pdf/commondec2008eng.pdf ) ስንሰማ፥ አቡነ ጳውሎስን እንዲታዘቧቸው፥ “ከ አዳም ሰብአዊ በደል ውጭ” ወይም እነሱ እንደሚሉት “ያለ ጥንተ አብሶ” ተጸንሳ ተወለደች ማለት እመቤታችንን ከሰውነት ዘር ስለሚያወጣት፥ ቤተ ክርስቲያናችንም ከኦርቶዶክስነቷ ስለሚለያት አንቀበልም፥ እንዲያውም የሮማ ካቶሊክ ትምህርትና እምነት ነው በማለታችን፥ <u>ለስድስት አመታት ያህል በኛ ላይ የሚያደርሱትን ዘመቻ ገልጸን “ምን ትላላችሁ? ከተሳሳትን አርሙን” ብለን አኀት አብያተ ክርስቲያናትን ጠየቅን</u>:: እነሱም በመካከላችን በመገኘትም በደብዳቤም ትክክል እንደሆን መሰከሩልን፥ እንድንበረታም አጽናኑን:: የሰጡንን ምስክርነትና ድጋፍ ሲሰሙ እነዚህኑ ምንም ግንዛቤ የሌላቸውን በመጠቀም የዘለፋ ዘመቻቸውን በአኀት አብያተ ክርስቲያንም ላይ ወንጨፉ:: የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ምሩልን አስተዳድሩልን እንዳላልን እየታወቀ፥ ጠልሰመኛውና መሰሎቹ “የኮፕቲክ ቤተ-ክርስቲያን ታዛዥ እንዳይደለች ማስታወስ ይገባቸዋል” እያሉ ነገሩን ወደ ፖለቲካ ቀየሩት:: የአቡነ ጳውሎስ ግብጽ ድረስ መሄድ እንደበረከትና እንደቅድስና እየቆጠሩ፥ የግብጾችን ወደ እኛ መጥተው ስለ ኦርቶዶክስ እምነትና ትምህርር መመስከር እንደተገዥነት በመቁጠር ርካሽ ፖለቲካቸውን ማሰራጨት ጀመሩ:: በሕዝብ የተመረጣችሁ የዲሲ ቅድስት ማርያምና ያካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ! ይህን ሁሉ እያያችሁና እየሰማችሁ ለዚህ አይነት ክህደት፥ ሽፍጥና ተንኮል መሣሪያ የሆኑትን እንደነ ደፍተራ ገለፈቶችን አቅፋችሁ መያዛችሁ በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ የስጠይቃችኋል::

በዚሁ አንቀጽ ላይ *“በሌላ ረገድ የኮፕቲክ ቤተ-ክርስቲያን ታዛዥ እንዳይደለች ማስታወስ ይገባቸዋል”* ይለናል:: አባቶቻችን ቤተ ክርስቲያናችንን ከግብጽ ሲኖዶስ ነጻ አድርገው የራሷ ሲኖዶስ እንዲኖራት ያደረጉት “የተጠራችሁለትን ነጻነት፥ ለሥጋችሁ ፈቃድ ማርኪያ ለማድረግ ሳይሆን እርስ በርስ በመዋደድ የፍቅር ተገዥ እንድትሆኑ” (ገላ ፭፡ ፲፫) እንዳለው በጣሊያን እነ አቡነ ጴጥሮስ ሲገደሉ፥ ግብጻዊው አቡነ ቄርሎስ የጣሊያኖችን ፈቃድ አስፈጻሚ ለመሆን ኢትዮጵያንን ቤተ ክርስቲያናችንን በመካዳቸው፥ ለሕዝቡ እንደነ አቡነ ጴጥሮስ ያሉትን ለማፍራት እንጅ እንደ <u>አቡነ ጳውሎስ</u> ያሉትን <u>የሲኖዶስ መሪና ለሮማ ካቶሊኮች ትምህርትና እምነት ጥብቅና ቆመው</u> የተዋሕዶውን እምነት እያወገዙ ቤተ ክርስቲያን የሚዘጉትን እንደነ አቡነ ማትያስ ያሉትን ለመፍጠር አልነበረም::

አቡነ ጳውሎስ "በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ፥ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ስበኩ" (ማቴ ፲፡፳፯) የሚለውን የክርስቶስን ትእዛዝ ክደው ራሳቸው የጻፉትን እንኳ ሳይቀር ደብቀዋል:: "ስለ እምነታችሁ ስትጠየቁ ለመመለስ ተዘጋጁ" (፩ኛ ጴጥ ፫፡፲፭) የሚለውን የቅዱስ ጴጥሮስን ትምህርት ሰርዘው ቤተ ክርስቲያናችን የምታምንበትን ለመመስከር አፍረዋል:: "በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፥ በሰው ፊትም የሚክደኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በባቴ ፊት እክደዋለሁ" (ማቴ ፲፥ ፴፪፡ ፴፫) የሚለውንም ጭራሽ ሰርዘው ለሹመቱ፥ ለንዘቡ ለራሳቸው ሐውልትና ለፖለቲካቸው ሽንጣቸውን ገትረው ሲታገሉ፥ የተዋሕዶውን ነገረ መለኮት ለመመስከር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሁላችንንም አሳፍረዋል::

አባቱ ነኝ የሚሉትን የተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታይም ለመከራውና ለጭንቁ ጊዜ አብረውት ሊቆሙ ቀርቶ በሐሰት ግዝታቸው ከሳቸው ጋራ ተባብሮ ሌላውን ወገኑን 'የማርያም ጠላት' ብሎ ቀጥቅጦ እንዲገለው አድርገዋል:: የሊቃውንቱን ጉባዔ አዳክመው፥ ጠንካራውንና የቤተ ክርስቲያናችንን መሠረተ ትምህርት ይዞ በአገር ውስጥና በዓለም ይንቀሳቀስ የነበርን የሃይማኖተ አበውን ድርጅት አፍርሰው፥ በምትኩ የቤተ ክርስቲያናችንን የነገረ መለኮት ትምህርት አሽንቀጥረው ጥለው፥ በስሜት ላይ በተመሠረተ የእምነት ጎዳና የሚነጉዱትን ወጣቶችች በተለያዩ የማኅበራት ስሞች አደራጅተው እርስ በእርስ እንዲፋጁና እንዲንጫጩ በማድረግ፥ ፍጅታቸውንና ጫጫታቸውን ለፖለቲካቸው ሽፋን አድርገው ተጠቅመውበታል::

የከንሳስ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን፥ በዚህ ዘመን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ነገረ መለኮት ዋቢ እንዳጣና፥ እንዲያውም ለፖለቲካ መከፋፋይ መጠቀሚያ እንደሆነ ታዘቡ፥ ለኛም ጸልዩልን የምስክር ቃላችሁም አይራቀን ብላ ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናትን በመጠየቋ *"ከወቅታዊ ፖለቲካ ጋራ አያያዙት"* እየተባለ በነ ደፍተራ ገለፈት ተዘመተብን:: ደፍተራ ገለፈት እንቀበላት፥ እንከተላት እያለ ወደ ሚናገርላት ወደ ሮማ ካቶሊክ መሄድ ነበረብን? ወይስ እነ አቡነ ጳውሎስ በማኅበረ ቅዱሳን ላይ እንዳደረጉትና፥ እርስ በርሳቸውም በጥቅም ሲጣሉ እንደሚያደርጉት ወደ አቶ መለሰ መሄድ ነበረብን? ወደ ሚመስሉን አብያተ ክርስቲያናት ጉዳዩን ማቅረባችን፥ አካሄዳችን ስሕተት ነበርን? ዜግነታችንን ወደ አኀት አብያተ ክርስቲያናት አገር ዜግነት እንደለወጥን ተደርጎ ሊነገርብን ይገባልን?

ይህች ጦማር ደርሳችሁ የምታነቡ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሆይ? አካሎቻችሁ ነንና ከተሳሳትን ፍረዱብን! ኢትዮጵያውያን የተሰበሰቡባት አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሁሉም አካል ናትና እነ ደፍተራ ገለፈት የሚሰነዝሩብን ወቀሳ ትክክል ከሆነ ሁላችሁንም ዝቅ አርገናልና ገስጹን! ለመሆኑ *"የራሷ ቅዱስ ሲኖዶስ ያላት ነጻ ቤተ ክርስቲያን"* ትሁን፥ ነገረ መለኮቱን ለሕዝብ መከፋፍያ አታድርጉት፥ እርስ በርሳችን እንድንከፋፈል አታድርጉን ማለት ፖለቲካ ነውን? ስንነጋገር፥ የመነጋገሪያችን መሠረትና መለኪያችን ቅዱስ መጽሐፍ መሆን አለበት:: ደፍተራ ገለፈት በኛ ላይ የሰነዘረውን ክስ በቅዱስ መጽሐፍ ስንለካው፥ ዳዊት የኦርዮን ሚስት ደፍሮ፥ ኦርዮንንም ባስገደለበት ጊዜ በጥጉ የነበሩት ካህናት ሳዶቅና አብያታር አፋቸውን ይዘው ተቀመጡ:: ናታን የተባለው ነቢይ ግን "ነፍሰ ገዳዩ አንተ ነህ" እያለ በዳዊት ላይ ጮኸ:: የከንሳስ ደብረ ሣሕል መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ጨኸች ከናታን ጨኸች ጋር ተቀራረበ:: ታዲያ ናታን እውነቱን በመናገሩ የፖለቲካ ሰው ሆኖ ሊወቀስ፥ በዳዊት ዙሪያ የነበሩት ካህናት

*ደግሞ ዝም ስላሉ የመንፈስ ሰዎች ነበሩ ተብለው መወደስ ይገባቸዋል ሊለን ነውን?* (መጽ ሳሙ ካልዕ ምዕ ፲፪-ምዕ ፲፫):: በዚህ አንጻር የከንሳስ ደብረ ሣህል ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነገረ መለኮቱ ተዘነጋ፥ መንፈሳዊነት ወደቀ እያለች በመጮሁዋ *"ከወቅታዊ ፖለቲካ ጋራ አያያዘችው"* ተብላ መወቀስ ይገባታልን?

# ፬ኛ ራሱ 'መናፍቅ' ሆኖ ሳለ ሌላውን 'መናፍቅ' ወይም 'ጎራ (cult)' ብሎ ስድብ አዘል ምክር ለጋሽ መሆን

*"ውጉዝ ካህን በመከተል በአሉት ላይ ሌላ የመናፍቅ ጎራ (cult) ከመፍጠር በስተቀር የሚጠብቁትና የሚያስጠብቁት እምነትና ትውፊት እንደሌለ በጥሞና ሊረዱት እንደሚገባ መገንዘብ አለባቸው"* በማለት ይቃዣል:: እኔ አልተወገዝኩም ያወገዘኝም የለም:: እንኳን እሱ አቡነ ማትያስም ለስድስት ወር አገድኩ አሉ እንጅ አወገዝኩ አላሉም:: ከኦርቶዶክስ ነገረ መለኮት ውጭ የሆነው ሠርጎ የገባው የሮማ ካቶሊኮች እምነትና ትምህርት ለሰባት አመታት ባገለገልኩባት በከንሳስ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ስላመጡብን በተፈጠረው ያለመግባባት፥ እነዚሁ ክህደቱን ያመጡት ግለ ሰቦች አቡነ ማትያስ መጥተው ይመስክሩልን በማለታቸው አቡነ ማትያስ ወደ ከንሳስ መጡ:: የኦርቶዶክሱን ነገረ ማርያም አበጥረው በማስተምር ፋንታ፥ አንድ ጊዜ ወደ ቡድሐ ሌላ ጊዜ ወደ ካቶሊክ በመዝለል ከሰንበት ተማሪዎች በባሰ ሁኔታ ወደቁ:: እኔ "የተጋበዙት የኦርቶዶክሱን ተዋሕዶ እምነትና ትምህርት ለመመስከር ነው፥ ይህ እርሰዎ የሚከተሉት የኦርቶዶክስ አይደለም:: ቦታወም አይደለም" ስላቸው፥ ያልኩበትን አብራራልኝ ማለት ሲገባቸው አግጃለሁ ብለው የጻፉትን ለሕዝብ አነበቡ:: ከሊቃውንት አበው ከተማርኩት፥ እንድጠብቀውም ከተካንኩለት ነገረ መለኮት እንዲሁም ከምዕመናኑ አዕምሮ በላይ በተሳሳተ እምነትና ትምህርት ለመጡት ለአቡነ ማትያስ ክብር መስጠት ኃጢአት ስለሆነ፥ እዚያው እሳቸው ፊት "እኔ የምነግራችሁ የእናትና የአባቶቻችሁ እምነት ሆኖ ባታገኙት ከምላሴ ጻጉር" ብየ ለምዕመናኑ ለመናገሬ በቦታው የነበሩት የከንሳስ ምእመናን ምስክሮቼ ናቸው::

ያም ሆነ ይህ ያች ወቅት በኔና በአቡነ ማትያስ መካከል የነበረውን ትልቅ ልዩነት ያንጸባረቀች በመሆኗ ሊቀ ጳጳስ ስለተባለ የቤተ ክርስቲያናችንን ነገረ መለኮት አለማወቁን፥ ቄስ ስለተባለም ከሊቀ ጳጳሱ አለማነሱን እንዲያውም ነገረ መለኮቱን ጠብቆ ለማስጠበቅ በልጦ መገኘቱን እውነተኞች ክርስቲያኖች የተገነዘቡባት ነበረች:: ስለገረ መኮቱ ምንም ግንዛቤ ሳይናራቸው ወደ ጵጵስናው በመጡ

ሰዎች ቤተ ክርስቲያናችን እጅግ የተጎዳችበት ዘመን እንደሆነ ብዙዎቻችን የተገነዘብንባት ወቅት ነበረች ብል ማጋነን አይሆንብኝም::

ምእመናኑ፥ እንኳን ጳጳስ፥ ተራ ዲያቆንም ቢሆን ከቤተ መቅደስ ሲገባ ሲወጣ ካዩ፥ ስለሃይማኖቱ ከነሱ የበለጠ ያውቃል ብለው ይገምታሉ:: በዚህ ግምታቸው እኔ የተናገርኩትን እውነትና በአቡነ ማትያስ የሚነገራቸውን ስሕተት የሚመዝኑበት ችሎታ ስላልነበራቸው ከችግር ላይ ወደቁ:: ነፍሳቸውን ይማርና አቡነ ይስሐቅ ጉዳዩ በዲሲ ማኅበረ ካህናት እንዲታይ አደረጉ:: በወቅቱ በዲሲ ዙሪያ የነበረው ማኅበረ ካህናት አቡነ ይስሐቅና አቡነ ገብርኤል በተገኙበት፥

፩ኛ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ

፪ኛ ቆሞስ አባ መአዛ በየነ

፫ኛ ሊ/ማ/ዶ/አማረ ካሣየ

፬ኛ ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

፭ኛ መጋቤ አዕላፍ መክብብ አጥናው

፮ኛ አባ ሠረቀ ብርሃን ወ/ሳሙኤል

፯ኛ ሊቀ ኅሩያን ከፈለኝ ወልደ ጊዮርጊስ የቃለ ጉባዔው ጸሐፊ በመሆን ስብሰባው ቀጠለ:: የካህናቱ ጉባዔም ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በፍቅርና በመግባባት ጉዳዩን ለማየት እንዲያመች

፩ኛ አቡነ ገብኤልን
፪ኛ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህን
፫ኛ መጋቤ አዕላፍ መክብብ አጥናውን
፬ኛ የቃለ ጉባዔውን ጸሐፊ ሊቀ ኅሩያን ከፈለኝ ወልደ ጊዮርጊስ

የቃለ ጉባዔውን ጸሐፊ ሊቀ ኅሩያን ከፈለኝ ወልደ ጊዮርጊስን ወደ አቡነ ማትያስ ላከ::

ልኡካኑም "ቀሲስ አስተርአየ ባገዷቸው መሠረት እገዳውን አክብረው እስከ ዛሬ ብትእግስት ይገኛሉ:: ይህም ታዛዥነታቸውን ያሳያል ሁላችን እንደምናውቀው እገዳ ቀርቶ ውግዘትም እየተጣሰ አገልግሎት የሚሰጥበት ሁኔታ ውስጥ መኖራችንን እንገነዘባለን .... እኚህ ሰው ተራ ሰው አይደሉም ያውቃሉ የተማሩ ብዙ ያወቁ ብዙም የሚጽፉ ናቸውና ወደእልክ የሚያስገባ ነገር ከመጣ ችግሩ ይብሳል" ሲል ለአቡነ ማትያስ የሰጠው ማሳሰቢያ በቃለ ጉባዔው ሰፍሯል:: አቡነ ማትያስም፥ ቀሲስ አስተርአየ "ቅዳሴ ለመቀደስ ሕብስት በጻሕል ወይን በጽዋዕ መሰየም አለበት፥ እመቤታችንም በአዳም ከነበረው ቁርኝት የተቀደሰችው መጀመሪያ ወደ ህልውና መምጣት ነበረባት" ብሎ የሚያምነውን ቀይሮ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቷ በፊት ተቀደሰች የሚለውን ካልተቀበለው እግዳውን አላነሳም አሉ:: ልኡካኑ በአቡነ ማትያስ አዝኖ ከተመለሰ በኋላ፥ አቡነ ገብርኤል "አቡነ ራሱማትያስ አገድኩ እንጅ አወገዝኩ አላሉም፥ ከእገዳ ይልቅ ውግዘት አይከፋምን? ለመሆኑ ያልተወገዘ አለ? እራሳቸው አቡነ ማትያስ ጽጽስናውን በሰጧቸው በአቡነ ተክለሃይማኖት ተወግዘው ለአሥር አመት ዝም ብለው ሲቀድሱ ኖረው የለም! ተመልሰህ ዝም ብለህ አገልግሎቱን ቀጥል" የሚል ሐሳብ አመጡ:: እኔም "ወደ ዚህ የመጣሁት እግዳውን አምኜበት እንድታነሱልኝ አይደለም:: ይህንንማ እዚያው በአቡነ ማትያስ ፊት ለከንሳስ ምዕመናን ገልጫለሁ፡፡ አቡነ ማትያስ ቢሳሳቱም፥ በእዚአብሔር ቤት ይቅርና፥ በባሕላችን አንዱን አንዱ በእግዚአብሔር ይሁንብህ አቁም ቢለው፥ ዝም ብሎ ጥሶ መሄድ ነውር ነው::እንዲአቆም የተጠየቀው እስኪጣራ ድረስ መቆም አለበት" የሚል መልስ ነበር የሰጠሁት::

የካህናቱ ጉባዔም፥ መጻሕፍትን መርምሮ፥ የግብጹ ፓትርያርክና ራሳቸው አቡነ ጳውሎስም በእንግሊዘኛ የጻፉትን ተረድቶ፥ "ከጊዜ በኋላ የመጣውና ሕዝበ ክርስቲያኑን በመከፋፈል ላይ ላለው እንግዳ ትምህርት ቅድሚያ በመስጠት ችግሩ በየቦታው እየተዛመተ በቤተ ክርስቲያናችን መለያየትን እያስፋፋ እንዳይቀጥል:: በተለይም እስከ ዛሬ ወልድ ዋሕድ በማለት አንድ ሆነን ከኖርነው ከአራቱ አኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋራ ያለንን የነገረ ሃይማኖት አንድነት እንዳያስቀርብን ብሎም እንዳይለያየን. . . እናት ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምሮ ስትጠቀምበት የነበሩትን ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቀድሞ ሊቃውንትን እምነት ባገናዘበ ሁኔታ የማያዳግም ውሳኔ ይስጥበት" ብሎ ለጥናት ከቀረቡት የመጻሕፍት ስም ዝርዝርና ከሊቃውንቱ ማስረጃ ጋራ በጉባዔው ሰብሳቢ <u>በሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ኃይሌ ፊርማ</u> ለቅዱስ ሲኖዶስ ላከ::

በአቡነ ማትያስ እገዳ ለተቸገሩት ለከንሳስ ኪዳነ ምህረት ምእመናንም፥ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሥራች አባት የነበሩት አቡነ ይስሐቅም፥ "በዚህ ጉዳይ በተፈጠረው ችግር ምክንያት የሻከረውን ሕልናችሁን የደፈረሰውን መንፈሳችሁን በቤተ ክርስቲያናችን እምነትና በቅዱሳት መጻሕፍት አስተካክላችሁ በተዋሕዶው እምነታችሁ በመቆም ከዚህ ቀደም በነበራችሁ ፍቅርና አንድነት ጸንታችሁ የተቋረጠውን አገልግሎት ካገልጋያችሁ ካህን ከቀሲስ አስተርአየ ጋራ ይህ ደብዳቤ ከደረሳችሁ ቀን ጀምሮ እንድትቀጥሉ ባለኝ ኃላፊነት አሳስባችኋለሁ" ብለው ሕዳር ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. በሰጡት መመሪያ ወደ ከንሳስ ተመለስኩ::

<u>አቡነ ገብርኤልም</u> ልደታ ለማርያም ብለው በከፈቱት ቤተ ክርስቲያን <u>"ዜና ልደታ"</u> ተብሎ ይዘጋጅ በነበረው ጋዜጣ፥ ግንቦት ወር ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.፥ ጥንተ አብሶን በተመለከተ የሚከተለውን አሉ::"ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በዝማሬው ያስተማረውን ትምህርት እንከተላለን:: ትምህርቱም እንዲህ የሚል ነው:: ". . . አንጺሆ ሥጋሃ ኀበ ማርያም ኀደረ፥ ቀዲሲ ኪያሃ ኀበ ማርያም ኀደረ፥ መለኮቶ ወልድ ውስተ ሥጋሃ ደመረ" (ዕዝል ዘግንቦት ደብረ ምጥማቅ) ማለትም፥- <u>"ሥጋዋን አንጽቶ፥ እርሷንም ቀድሶ ከማርያም ዘንድ አደረ"</u> ብለው አስተምረዋል::

አቡነ ጳውሎስና ሲኖዶሱ ለሃይማኖቱ ቅድሚያ ሰጥተው እስከ ዛሬ ድረስ መልስ ባለመስጠታቸው፥ ደፍተራ ገለፈት ይህችን አጋጣሚ ተጠቅሞ ለፍቅር ነዋይ ያለውን ፍላጎት ለማርካት፥ *"ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት"* በሚል ርእስ ውጉዝ ካህን እያለ ይህችን መፈክረ ሰይጣን ለንግድ አዘጋጀ::

ከላይ እንደገለጽኩት እኔን <u>ሳልወገዝ 'እገዳው'ን 'ውግዘት'</u> ካለው፥ <u>በብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተወግዘው እስከዛሬ ድረስ ውግዘቱ ሳይፈታ ሊቀ ጳጳስ እየተባሉ የሚኖሩትን አቡነ ማትያስን ምን ሊላቸው ነው?</u> የከንሳስ ደብረ ሣሕልን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን (cult) የመናፍቅ ጎራ ካላትስ፥ እሱን የመሰሉ ጸረ ቤተ ክርስቲያንና ምዕመናን ከቤተ ክርስቲያናችን ይውጡልን እያሉ የሚጮሁባቸውን ዘማውያን የተሰበሰቡባትን የዲሲ ቅድስት ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ምን እንበላት? እናንተስ የሕዝብ አደራ የተቀበላችሁ የቦርድ አባላት ቢህች ቤተ ክርስቲያን የሚነገረውን ጆሯችሁ እየሰማ አይናችሁ እንዴት ዝም አላችሁ?

በገጽ 108 ላይ *“ወልዳ ያሳደገችውን እናት ገበና ለመግለጥና ዓይኗን ለመጓጎጥ የሚደፍሩና የሚጨክኑ መናፍቃን የተሐድሶ ጎራዎች ናቸው”* ይላል:: ይህች አረፍተ ነገረ እኛን የማይመለከቱ ሶስት ሐረጎች አዝላለች:: ፩ኛ “ገበና መግለጥ፥ ፪ኛ ዓይን መጓጎጥ፥ ፫ኛ የሚጨክኑ መናፍቃን የተሐድሶ ጎራዎች” ያላቸው ናቸው:: ለመሆኑ ገበና ምንድን ነው? ገበና የማይገለጥ፥ የተደበቀና የተሰወረ፥ ቢገለጥ ግን የሚያሳፍር ነገር ነው:: ጌታችን “የማይገለጥ የተከደነ የማይታወቅ የተሰወረ ምንም የለም”( ማቴ ፲፡፳፮) እንዳለው፥- ከጊዜ በኋላ እሱ *“ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት”* እያለ የሚጠለስመውንና መሰሎቹ እነ ደፍተራ ሀብተ ማርያም ተድላ፥ እመቤታችንን ልክ ባንድ ዛፍ ላይ እደበቀለች ተገድራ አርገው በአዳም ገላ የነበረች ነጭ እንቁ እያሉ የሚያሰራጩትን ጸረ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት፥ የቤተ ክርስቲያን ገበና ካላለው በስተቀር ቤተ ክስቲያናችን ገበና የለባትም:: እሱና መሰሎቹ የሚያሰራጯቸውን መፈክረ ሰይጣን ገልጦ ለማስረዳት የሚደረገው ጥረት፥ ከቤተ ክርስቲያናችን ዐይን የገባውን ጉድፍ ማስወገድ እንጅ እሱ እንደሚለው የቤተ ክርስቲያንን አይን መጓጎጥ አይደለም:: ጌታችን “እፎ በእከ ካልዕየ ዘኢለብከ ልብሰ መርዓ ... አዘዘ ንጉሥ ለገዛዕት ይእስርዎ እደዊሁ ወእገሪሁ ወያውጽእዎ ውስተ ጸናፌ ጽልመት ሀበ ሀሎ ብካይ ወሐቀየ ስነን” (ማቴ ፳፪፡፲፩-፲፫):: እንዳለው፥ ማለትም “በዝግጅቱ ላይ ለመገኘት ዝግጅቱ፥ በታውና ሥርአቱ እንዲያሟላ የሚጠይቀውን ሳያሟላ መስሎ የገባውን ሠርጎ ገብ እጅግሩን አስራችሁ ልቅሶ ወዳለበት፥ ጥርስ ወደሚፋጭበት ጨለማ ውስጥ ጣሉት” እንዳለው እኛም የኦርቶዶክሶችን አበው ሕጸጽ አለባቸው እነሱን ተከትለን በጭፍን መሄድ አይገባንም ብሎ “ዓይን ገላጭ የሆነውን የላቲኖችን እንከተል” በማለቱ የቤተ ክርስቲያናችን ገበና እናንተ ደፍተራ ገለፈቶች ናችሁ ከቤተ መቅደሳችን ውጡ ማለታችን “ገበና መግለጥ፥ እና ዓይን መጓጎጥ፥ አይደለም::

የሮማ ካቶሊኮችን ቅዠትና ኑፋቄ አንቀበልም በማለታችን *“የሚጨክኑ መናፍቃን የተሐድሶ ጎራዎች”* ብሎናል:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ጽንኡ እስመ አነ ሞእክዎ ለዓለም” እንዳለው፥ ማለትም “እኔ ዓለምን ድል እንደነሳሁ እናንተም የሚደርስባችሁን መከራ ሳትፈሩ ድል ንሱ!” ባለው መሠረት ደፍተራ ገለፈቶች የሚያሰራጩትን አሉባልታና የስም ማጥፊያ ዘመቻ ሳንፈራ ቆመን መመስከራችን ያኮራናል እንጅ አያሳፍረንም::

“አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም” የተባሉትን የቤተ ክርስቲያኒቱን ዓይኖች *“ሕጸጽ አለባቸው መጻሕፍቻቸውንም መቀበል አንችልም አይገባንም”* እያለ፥ እኛ ሕጸጽ የለባቸውም እንቀበላቸዋለን በማለታችን *“መናፍቃን የተሐድሶ ጎራዎች ናቸው”* ካለን ለቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪ መስሎ የኛን ጬኸት በመቀማት ያዘውን እንባ ማንባቱን በግልጽ መረዳት የሚሳነው የለም:: ደፍተራ ገለፈት አንቀበላቸውም ያላቸው ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት “ወኮነ በሥጋሁ ሐዳሴ ዕጓለ እመሕያው”(ሃይ ምዕ፻፲፱፡ ቁ፪) ማለትም፥- “መለኮት በተወሐደው ሥጋ ለሰው ልጅ ሕይወት አዳሽ ሆነ” ያሉትን አረጋግጠን እናስተምራለን:: እንዲያውም ቅዱስ ጳውሎስ “በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን አድርጉ እንጅ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ እርሾም አይደለም”( ፩ኛ ቆሮ፭፡፰):: ባለው መሠረት፥ በክፋት፥ በግፍና በደል የላሸቀውን ጠልሰማዊ ሽፍጥ ከቤተ ክርስቲያናችን ለማስወገድ እንታገላለን:: “የሚጠፋውን አሮጌውን ሰውነት አስወግዱ፡ በአዕምሯችሁ መንፈስ ታደሱ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ”( ኤፌ ፬፡፳፫-፳፬) ባለው መሠረትም፥ ክርስቶስ

የእኛን አካል የእኛን ባሕርይ ከመለኮቱ ጋራ ባደረገው ውሕደት "ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላእሌነ" እያልን ሥጋውን በመብላት ደሙን በመጠጣት ሁላችንም ሁልጊዜ እንታደሳለን ብለን እናምናለን፤ እናስተምራለን:: "ኢይኩን ለርስሐት ወኢለኩነኔ አላ ለሐድሶ ነፍስ ወሥጋ ወመንፈስ" (የሐዋ ቅ. ገጽ ፻፲፩ ቁጥ ፻፵):: እያሉ ቅዳሴውን የማይቀድሱ ወንጌሉን የማይሰሙ ሥጋውንና ደሙን የማይቀበሉ ካህናትና ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ካሉ፥ ክርስቲያኖች አይደሉም:: እነደፍተራ ገለፈት ተሐድሶዎች ናችሁ እያሉ በሌላው ላይ ሲዘምቱ ቀርቶ፥ ቤተ ክርስቲያናችን "ጻኡ ንኡሰ ክርስቲያን" እያለች በነሱ ላይ የምታውጅባቸው ናቸው::

# ፳ኛ "አንዳንድ ምዕመናን ካህኑን አይሰሙትም"ይላል

*"አንዳንድ ምዕመናን ካህኑን አይሰሙትም"*:: ማለትም "ካህኑ በኃላፊነቱ የሚሰጠውን መመሪያ ለመቀበል ፈቃደኞች ሆነው አይገኙም" ይላል:: እውነት ነው! ምዕመናን መስማት ያለባቸው፥ ጌታችን "በጎቼ ቃሌን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ፥ እነሱም ይከተሉኛል" ባለው መሠረት ከክርስቶስ ትምህርትና ከቤተ ክርስቲያን እምነት ውጭ ጸረ ቤተ ክርስቲያን ትምህርትና ምክር አይቀበሉም መቀበልም የለባቸውም:: እውነተኞች ካህናት ይህንኑ ማስተማር አለባቸው:: "እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል" እነደተባለው እነ ቅዱስ ጳውሎስም "ተመሰሉ ኪያየ በከመ አነ እትሜሰሎ ለክርስቶስ" "(፩ኛ ቆሮ ፱፥፩) ማለትም፥ ምዕመናን "እኔ ክርስቶስን እንደመሰልኩት እኔን ምሰሉ" እያሉ የሚያስተምሩትን ኦርቶዶክሳውያን ካህናት ከመስማት ይልቅ እንዴት አሁን በቤታችን ሠርጎ የገባውን ትምህት የሚሰብኩትን እነደፍተራ ገለፈቶችን ይስሙ?

ደፍተራ ገለፈት *"አንዳንድ ምዕመናን ካህኑን አይሰሙትም"* ማለቱ ከዚህ ቀደም የደብረ ሰላም ቅድስት ማርያምን ምዕመናንን ለሁለት ለመክፈል፥ የራሱን ንግድ ለማካሄድ አፈሩንም፥ እምነቱንም፥ ጃንጥላውንም፥ ጧፉንም ከቁልቢ አምጥቼ የቁልቢ ገብርኤል ብየ ቤተ ክርድቲያን ከፍቻለሁ ባለበት ጊዜ፥ "አንቀበልህም አንሰማህም" ብለው ባንድነታቸው ጸንተው በመቆም ተቃውመውት ነበርና፥ ዛሬ አይሰሙም በማለት የሚከሳቸው እሱን ካልሆነ በቀር ሌላ ምን ያስተማረው ነገር አለና ምእመናኑ ካህኑን አይሰሙትም እያለ ይከሳል? የዲሲ ቅድስት ማርያም ምእመናንና የአስተዳደር ቦርድ አባልት ሆይ! ይህ ሁሉ የተፈጸመው እናንተ ባላችሁበት በዚህቹ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሆነ እናንተው ፍረዱ::

ይህ ይሉኝታ የሌለው ደፋርና ጨካኝ የሚናገረው እሱን አቅፈው ስለያዙት ስለ ዋሽንግተን ዲስ ቅድስት ማርያም ምእመናን ከሆነ የበደል በደልና ንቀት ነው:: ሃይማኖትና ይሉኝታ ቢኖረው ኖሮ፥ በትእግስትም ሆነ ባለማወቅ እንደሱ ያለውን ተሸክመው መኖራቸው ተገቢ ባይሆንም፥ ሊያደንቃቸው በተገባው ነበር:: ከዚያ አልፎ ሰርስሮ በመግባት የቦርድ ሊቀ መንበር እስከ መሆን በመድረስ፥ ቅዱሳን አበውን መናፍቃን ለማለት፥ መጻሕፍትን ለማጣጣልና ሰውን ሁሉ ለመናቅ በቃ:: በመጨረሻም አቁም የሚለው ጠፍቶ፥ እንዲያውም ከነ ዶክተር አክሊሉና አቶ ቢልልኝ ያላሰለሰ ድጋፍ በማግኘቱ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶን ነገረ መለኮትና ታሪካችንን ነቃቅሎ ጥሎ የካቶሊኮችን እንቀበል ማለቱን ቀጠለ:: በጭንቅላቱ የተሸከመው ክህደት መሆኑንና ራሱም የኦርቶዶክስ ካህን መስሎ መግባቱን፥ ለመጽሐፍ ቅዱሱ፥ ለነገረ መለኮቱና ለታሪካችን እንግዳ መሆኑን በራሱ አረጋገጠ:: ታዲያ እንደሱ የመሰሉትን ይሉኝታና ሃይማኖት የለሾችን፥ ቅንዝረኞችን ምእመናኑ ለመስማት እንዴት ፈቃደኞች ይሁኑ? “ምዕመናን ካህኑን አይሰሙትም” በማለቱ ይልቅስ <u>በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውን፥ የአባቶቻችንን በሃይማኖታቸው ጸንተው የሰሩትን የተቀደሰ ሥራ እንድናስታውስ አደረገን</u>::

# አባቶቻችን በደፍተሮች ላይ የወሰዱት የተቀደሰ ርምጃ፡-

፩ኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ቤቴ የጸሎት ቤት ናት እናንተ ግን የንግድና የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችኋት” በማለት በቤተ መቅደስ የማይገባ ሥራ የሠሩትን እንዳስወገዳቸው፥ <u>አጼ ቴወድሮስም</u> ቤተ መቅደስን ጥግ አርገው በጠልሰማቸውና ባሉባልታቸው እንደ ደፍተራ ገለፈት ሕዝቡን ያሳስቱ የነበሩትን ከቤተ መቅደስ አስወገዱ፥

፪ኛ በቦሩ ሜዳ ላይ የተሰበሰበው ሕዝብም “በማስመሰል ሰውን ሁሉ ስታስክዱ ኖራችኋልና ትቀጣላችሁ” በማለት፥ በአለቃ ሀብተ ወልድ፥ በአለቃ ውቤ፥ በአለቃ ቤተ ሌዊና በአለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ላይ ፈረዱ፥

፫ኛ አገራችን ኢትዮጵያ ከጣሊያን ጋራ በትንቅንቅ ላይ በነበረችበት ወቅት፥ አገሩንና ሕዝቡን ሃይማኖቱን ክዶ ለጣሊያን አድሮ የራሱን ሕዝብ ይሰልል የነበረውን አለቃ ታየ የሚባለውን ጠልሰመኛ ደፍተራ፥ በብቸና ሰኞ ገበያ ላይ በላይ ዘለቀ በሕዝቡ ፊት አጋድሞ መግገረፉንና የመሳሰሉትን ታሪካችንን አስታወሰን::

የአገራችን ገበሬዎችም እንደሱ ያሉትን ሐሰተኞች በአባያ በሬዎቻቸው ጆሮ ላይ በሚያጮኹት ጅራፍ “ወፈ ገዝት ደፍተራ” እያሉ እንደሚገርፉ እየሰማን አድገናል:: ይልቅስ ዛሬ ትልቅ ችግር የሆነው ከምዕመናን ገንዘብ በመዝረፍ፥ በመዋሸት ከዓለማውያን ጋራ ውድድር በመግባት ሕንጻ የሚገነቡትን፥ የሚቀላምዱትንና የሚዋሹትን አንዳንድ ጳጳሳትን መነኮሳትንና ካህናትን ተባብሮ በመነሳት አቁሙ ከማለት ይልቅ፥ በሐሜትና በትዝብት ሕሊናቸው እየቆሰለ አፋቸው የዘጉ ሰዎች መብዛታቸው ነው::

በዚሁ አንቀጽ *“የመታዘዝ ሚና ከመስዋእት ይበልጣል”* ይላል:: አዎ ይህ ቃል የእግዚአብሔር ቃል ነው:: ይሁን እንጅ ምእመናን ከመስዋእት የበለጠ ሚና ለመጫወት መታዘዝ ያለባቸው እሱ *“ቤተ ክርስቲያናችን አሁን በነገረ ማርያም ከእነሱ ብትለይ የሚያስፈራት ወይም የሚቀንስባት ምን ሊኖር ይችላል?”* እያለ ራሱ ለሚሰብከው ክህደት ሳይሆን፥ ከክርስቶስ ትምህርት፥ ከሐዋርያት ስብከት፥ ከኦርቶድሳውያን ሊቃውንት አበው ትውፊት ፈቀቅ ላላለው ለጥንታዊው ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ነገረ መለኮት ብቻ ነው::

*“ስደት ለውሸትና ለእምቢተኛነት አመች ሆኖ ስለተገኘ ሥርአተ ቤተ ክርስቲያን ለመጠበቅ አስቸጋሪ ሆኗል”* (209) :: ክርስትናም ሆነ ከክርስትና ውጭ የተጻፉ የታሪክ መጻሕፍት ስለስደት የሚነግሩን፥ ለተበደለ ሕዝብ፥ ለተገሰሰ እምነት ለመመስከር አምባሳደርነት ነው:: በክርስቲያኖች ዘንድ ስደት እውነት ለመመስከር የሚያመች ነው:: ጌታችን ከተወለዳባት መንደር ወደ ግብጽ ተሰደደ:: በመጨረሻም መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ ተሰደደ:: ከዚያም ሐዋርያትን የነገርኳችሁን ይዛችሁ እየመሰከራችሁ ተሰደዱ ነው ያላቸው:: ደፍተራ ገለፈት አልገባውም እንጅ የክርስትና መሠረቱ ስደት ነው:: አገሩም ዓለም ነው:: ይህችም አገር አሜሪካ የተመሰረተችው እየተሰደዱ በመጡ ሰዎች ነው:: ይህችን ዓለም በቴክኖሎጂ የለወጡ ብዙዎቹ ስደተኞች ናቸው:: እሱም ቢሆን የዛሬውን አናውቅም እንጅ ወደዚህ አገር ሲመጣ መንግሥት አምባሳደር አርጎ አልላከውም:: ቤተ ክርስቲያናችንም ልኡክ አርጋ አልላከቻቸውም:: የመጣው በስደት ነው:: ያም ሆነ ይህ፥ ከተወለዱበት አገር የሚሰደዱ ሐሰትን እውነት አስመስለው ሥርአት የሚአወጡትን የሚፋለሙ፥ የሐሰትን ሥርአት ለመጠበቅ ለተሰለፉ ሁሉ ደፍተራ ገለፈቶች ልብ ላይ የተተከሉ ሾተሎች መሆናቸውን መረዳት ይገባዋል:: ፍጹም ሕጸጽ የለባቸውውም ብለን በተቀበልናቸው፥ እሱ ግን በካዳቸው ከኪዳን ጀምሮ እስከ ቅዳሴያችን ድረስ ባሉን መጻሕፍት ለእውነት መሰደድ የሚደገፍ ነው::

ለምሳሌ መጽሐፈ ኪዳናችን “ዘይትዌከፎሙ ለእለ ይሰደዱ፡ ረዳኢ ወለእለ ውስተ ሠርም ይትመነደቡ መድኅን ለርኁባን ዘይሄሊ ወይትቤቀል ለግፉአን”(ኪዳን ዘሰርክ) ይላል:: ማለትም “ከአገራቸው የተሰደዱትን የሚቀበላቸው የሚረዳቸው፥ በመከራ ያሉትን የሚያድን ለተራቡ የሚያስብላቸው ለተበደሉ የሚበቀልላቸው” በማለት ከተሰደዱት ጋራ ይሰለፋል::

መጽሐፈ ቅዳሴያችንም “በእንተ ስዱዳን ናስተበቁዕ ከመ እግዚአብሔር የሀቦሙ ትእግስተ ወትምህርተ ሠናየ ወይጸጉ ጻማሆሙ ፍጹመ” (ዳሴ ገጽ ፺፫፡ ፺፩) ይላል::ማለትም “ትዕግስትን በጎ ትምህርትንም ይሰጣቸው ዘንድ የድካማቸውን ፍጹም ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ ስለ ተሰደዱ ሰዎች እንማልዳለን” በማለትም የተሰደዱት ሁሉ በተሰደዱበት ባእድ አገር ትምህርትን በጎ ልምድን ጥበብንና ማስተዋልን እንዲሰጣቸው፥ ለተሰደዱለት የተቀደሰ አላማ ጸንተው በመቆም ሊሚቀበሉት ዋጋ የበቁ እንዲሆኑ ይማልዳል::

በቅዱስ አትናቴዎስ የተዘጋጀው መጽሐፈ ቅዳሴም “ንሕነሰ እለ ተሰደድነ በእንተ ስምከ ወኮነ ሕብልያ እም ኀቤሆሙ ለእልዋን ረሰየነ በሣህልከ ከመ ነሐድፍ ልቦሙ ለመሃይምናኒከ” አትና( ገጽ ፪፻፴፭፥ ፪፴፰) ማለትም፡- “ስለስምህ የተሰደድን በዐላውያን ዘንድ ብዝበዛ የሆነ እኛን ግን በይቅርታህ

ጠብቀን የምዕመናን ልቡና እናጸና ዘንድ" እያለ ስለ ነገረ መለኮቱ የተሰደዱ ካህናት የተሰደደውን የምዕመናን ልቡና ለማጽናት ሕሊናቸው እንዳይሰለብ እንዲጸልዩ ያሳስባል:: ይህን መረዳት ቀላል ባይሆንም፥ በስደት የተወለዱ ኢትዮጵያውያን ሕጻንት እንኳ የሚአውቁትን

ነፍሷን ይማርና

"ካላጡ ካልተቸገሩ፥

መኖር ማን ይጠላል ባገሩ"

እያለች ማንአሕሎሽ ዲቦ ርቆ የተሰደደውን ወገኗን በመንፈሷ አሻግራ እያየች በውዝዋዜ የገለጸችውን፥ በድምጿ ያንጎራጎረችው እንዴት ማስተዋል አቃተው? አገሪቱ ያፈራቻቸው ሊቃውንቱ፥ በህክምና በሕግ፥ በመሐንዲስነትና በሌሎች ሁሉ የሰውን ሕይወት ወደተሻለ ሁኔታ በሚለወጡ ሙያዎች የበለጸጉ ሁሉ ዜጎች አገራቸውን ጥለው በዓለም የተበተኑት ከሕዝባቸው ይልቅ የማያውቁትን ሕዝብ ለማገልገል መርጠው አይደለም:: በጠበንጃ ኃይል ሥልጣን ከሕዝቡ የነጠቁ ጥራዝ ነጠቆች የዘረጉት ሥርአት ከሙያቸውና ከሕዝባቸው ጋራ ሊአገናኛቸው ባለመቻሉ ነው:: ይሁን እንጅ ደፍተራ ገለፈት የሥርአቱን ሽባነት ደብቆ፥ የተሰደደውን ሊከስ የሞከረ አድር ባይ ሽፍጠኛ ነው::

ስደት ለወሬ ምቹ የሆነው ተሰደው ከወጡ በኋላ ለሥጋዊ ደህንነታቸው የዜግነታቸውን መለወጥ ዋስትና አድርገው፥ የተሰደደቡት ምክንያት መፍትሔ ሳያገኝ ለግል ጥቅም ፍለጋ ለሚመላለሱ ሰዎች ነው:: ይህን ስል "የገበያ ግርግር ለቀጣፊ በጀው" እንዲሉ ከተፈጠረው የፖለቲካ ግርግር የሚያገኙትን ግላዊ ጥቅም ለሚያሳድዱ እነደ ደፍተራ ገለፈትን ለመሳሰሉ እንጅ በአገርና በወገን ናፍቆት ተገደው የሚሄዱትን ወገኖች አይጨምርም:: አንዳንዶች በተለይ መነኮሳት ከኢትዮጵያ ወደውጭ ሲወጡ የእውነተኛዎችን ስደተኞች ጩኸት በመጠቀም የምዕራቡን መንግሥታት አታለው የስደተኛነትን መታወቂያ ያገኛሉ:: ለዜግነት የምታበቃቸውን ሰዓት ይጠብቁና የምዕራቡን ዜግነት ተሻምተው ይወስዳሉ:: ከዚያ በኋላ በኮሚኒቲና በቤተ ክርስቲያን በተሰባሰበው ወገን መካከል ወዲያ ወዲህ እያሉ "እናንተ በሁለት ቢለዋ የምትበሉ ቀጣፊዎች" የማይል ሞራለ ቢስ ከሆነው መንግሥት ጋር ይሸፋፈጣሉ:: ይህ ሁኔታ ሃይማኖት የሚንድ፥ ታሪክ የሚያፋልስ ሐሰትና ክህደት የተሸከመ ጠልሰም እያሳተሙ የምዕመናንን ኪስ ለሚያሟጥጡ ለነደፍተራ ገለፈት ተመችቷቸዋል:: በታኝ የሆነውን ሥርአት የዘረጋውን አካል መንቀፍ፥ ሥርአቱን መተቼት የካህን ተቀዳሚ ተግባር መሆን ሲገባ፥ "ስደት ለውሸትና ለእምቢተኛነት አመች ሆኖ ስለተገኘ ሥርአተ ቤተ ክርስቲያን ለመጠበቅ አስቸጋሪ ሆኗል" ለሚል ለዚህ አይነት ደፍተራ ከፍተኛ ድጋፍ የሰጡትን እነ ዶክተር አክሊሉንና አቶ ቢልልኝ ማንደፍሮን ከሐፍረትና ከውርደት አዘቅት ውስጥ እንደጣላቸው ሊሰማቸው ይገባል::

ስደት ሊነቀፍና ሊተች የሚገባው የተሰደደ ሰው ከተሰደደ በኋላ፥ ትቶት ለወጣው ሕዝብና እምነት ወኪል ሆኖ በየደረሰበት ችግሩንና ሥቃዩን በትክክል የማይመሰክርና ተልእኮውን የረሳ ቁራ መሳይ መልእክተኛ ለሆነና፥ በተሰደደው ሕዝብ መካከል ተደብቆ "የላይ ደፋሪ የታች ፈሪ" እያለ በማያውቀው ነገረ መለኮት እየገባ ወገንን ለሚያተራምስ ለአቶ ቢልልኝና ለመሰሉ ሰዎች ሲቀጸል ብቻ ነው::

የስደተኞች መጠጊያ ናት እየተባለ ሲሰበከብባት በነበነበረችው በዲሲ ቅድስት ማርያም አውደ ምሕረት ላይ፥ የእነ አቡነ ጳውሎስን ሕጋዊነት፥ የሌላውን ሕግ ወጥነትና የሮማ ካቶሊክን ትምህርት እንቀበል እያለ የሐሰትና የክህደት ማሰራጫ ካደረጋት ደፍተራ ጋራ መተባበር ታሪክ ይቅር የማይለው ኃጢአት ነው::

ደፍተራ ገለፈት *"ስደት ለውሸትና ለእምቢተኛነት አመች ሆኖ ስለተገኘ ሥርአተ ቤተ ክርስቲያን ለመጠበቅ አስቸጋሪ ሆኗል"* እንዳለው፥ በማወቅም ይሁን ባለመገንዘብ ሰርጎ የገባው የጣሊያኖች እምነት ሠርጎ መግባቱን በነገረ መለኮቱ ትምህርታችን መሠረት ይታረም ብለን፡-

፩ኛ የጉባዔውን ትምህርት

፪ኛ በቤታችን ያሉትን መጻሕፍት

፫ኛ እራሳቸው አቡነ ጳውሎስ የጻፉት

፬ኛ የመላ ኦርቶዶክች እምነትና ትምህርት

፭ኛ ያለ ጥንተ አብሶ ተወለደች ብላ የምታምነው የሮማ ካቶሊክ ብቻ መሆኗን

የሚገልጽ የጽሁፍ ማስረጃ አገር ቤት ላለው ለሲኖዶስ ልከን ሳለ እስከ ዛሬ መልስ ያልተሰጠበትን ጉዳይ፥ መልስ ተሰጥቶበታል እያለ ያደናግራል:: **አብቀወ አፉሁ!**

ማኅበረ ካህናቱ ያቀረበው ጥያቄ፥ የተጠየቀው አካል በተገቢው መንገድ እንዲመለስ ከመተባበር ይልቅ፥ ግርግሩን ተጠቅሞ ንግድ ለማካሄድ አመች ሆኖ ስላገኘው ብቻ "ነገረ መለኮትን ታሪክን ሥርአተ ቤተ ክርስቲያን ለመጠበቅ አስቸጋሪ ሆኗል" እያለ መፈክሩን ማሰማት ጀመረ:: እንዲያውም ካቅሙ በላይ በመንጠራራት፥ ለእምነቱ የመሰከሩትን የአኀት አብያተ ክርስቲያናትንም ሳይቀር "የፓትርያርክ ሽኖዳ ሐሳብ ለማስረጃ የቀረበው እንደ ካቶሊኩ ፓፓ እሳቸውም የማይሳሳቱ ስለሆኑ ነው?" ገጽ 194 :: እያለ በስድ አደግ አፉ ዘለፋውን ቀጥሏል:: የሚናገረውን የማያውቅ የአቡነ ሽኖዳን ምስክርነት እነቅፋለሁ ብሎ እንቀበላቸው እያለ የሚሰብክላቸውን የሮማውን ፓፓ ለማይታመን ምስክርነት "እንደ" በማለት ንጽጽር አድርጎ አቀረባቸው:: አርፈው የተቀመጡትን ሁሉ አባቶች እያነካካ ስንቱን እንዳተረመሰው ተመልከቱ! ታዲያ ይህ ሰው ጤነኛ ነው ማለት ይቻላልን?

# ፯ኛ የጣሊያንን 'ማሪያማዊ ሕገ-ሃይማኖት' እንከተል እያለ የተዋህዶውን ሕገ- ሃይማኖት ባዕድና መሳለቂያ ያደርጋል አለ።

*፯ኛ "ሥፍራ እየቀያየረ ኑፋቄ ማራባቱን እንደ ጅብዱ የሚቆጥር ሰውን በየሄደበት መከተሉ በውጭ ያለነውን ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖችን እንድንከፋፈልና ለባዕድ ሃይማኖት ተከታዮች መሳለቂያ እንድንሆን ያደርጋል እንጅ ሌላ እርባና የለውም"* ይለናል። ከሐዋርያት ቀጥለው የተዋሕዶ ነገረ መለኮት ምስክሮች የሆኑትን ሊቃውንት አበውን አንመናቸው፥ መጻሕቶቻችንም አንቀበላቸው እያለ የቤተ ክርስርስቲያናችንን ሊቃውንትና ታሪካችንን ነቃቅሎ ከመጣልና፥ ራሱ የሚገረፍበትን ጅራፍ ከመፍተል ይልቅ ሥፍራ እየቀያየርኩ በቃልም በጽሑፍም ያሰራጨሁት ኑፋቄ ካለ፥ ለምን አያቀርበውም ነበር?

እኔ በጻፍኳቸውና ወደፊትም በምጽፋቸው ጦማሮች፥ ስም የጠቀስኩት እኮ! በግል ጥላቻ ወይም ሥጋዊ ጥቅምና ክብር ፈለጌ አይደለም። የተሳሳተውን አርሙ ብለን የጠየቅናቸው የሚመለከታቸው ሰዎች፥ ከማረም ይልቅ አፍነው ይዘው፥ ወደ ፖለቲካቸው ቀይረው እርስ በርሳችን እንድንጠፋፋበት ስላደረጉት ብቻ ነው። ነገረ መለኮቱ ያልገባቸው ለማደን ከዋሻው እንደወጣ ጅብ፥ ከገዳም እየለቀቀ ወደቀለጠው ከተማ የሚጎርፈውን ሁሉ ግሪን-ካርድ አዳኝ መነኩሴ ሳይቀር በላያችን ላይ ስለአዘመቱብን ነው። ወደ ሚመስሉን ኦርቶዶክሳውያን መስክሩልን ብለን ጉዳዩን ያቀረብነው በዚህ ሁሉ ተጽእኖ ምክንያት ስለጨነቀን ነው። አኀት አብያተ ክርስቲያናት እኛን አይዟችሁ በርቱ በማለት የእነ አቡነ ጳውሎስ አፍኖ መያዝ እያስገረማቸው በመነጋገር ላይ ሳሉ፥ እሱን የመሰሉ ደፍተራ ገለፈቶች በሙያው ሳይደክሙ የጠለቀ እውቀት ሳይኖራቸው ሕዝቡን እያታለሉ ከመኖራቸው ባሻገር፥ ራሳቸውን ከመላ ኦርቶዶክሳውያን ሁሉ በላይ አድርገው፥ ለእውነት የመሰከሩትን ሁሉ ለቡነ ጳውሎስ አለንለዎ ለማለት መዝለፍ ጀመሩ። የእምነቱ የታሪኩ ባለቤት የሆናችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ፍረዱ! ጉዳዩ ከአቡነ ጳውሎስ እጅ ደርሶ ከዚያም ለመላ ኦርቶዶክሳውያን ቀርቦ፥ የነደፍተራ ገለፈት እየዘለሉ በመካከል መግባታቸው አድርጉልኝ አልተባሉም ብሎ መገመት ይቻላል? ከተሳሳትኩ ፍረዱብኝ?

ከሽፍጥና ከአድርባይነት መንፈስ የተላቀቀ፥ በሞራል የላቀ፥ ነገረ መለኮቱን የተረዳና ያወቀ፥ ለታሪካችንና ለቤተ ክርስቲያናችን የተጠነቀቀ ቢሆን ኖሮ፥ የቅዱስ ዮሴፍን መጠራጠር ልክ መሆኑን በሊቁ በኤራቅሊስ ቃል እንዳረምኩ፥ እሱም ከተናገርኩት ሳይወጣ ቃል በቃል፥ ሐረግ በሐረግ፥ አረፍት ነገር

ባረፍተ ነገር፥ አንቀጽ በአንቀጽ እየጠቀሰ ወንድሜ ከዚህ ላይ ተሳስተሐል ቢለኝ ስሕተቴን አርሜ፥ እሱንም እንደመምሕር አክብሬ በተቀበልኩት ነበር::

ከምንም ተነስቶ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን አንድ ጊዜ ከፍ ሌላ ጊዜ ዝቅ በማድረግ፡ ከመላ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጋራ አጋጨ:: ሊቃውንት አበውን ከነ መጻሕፍቶቻቸው ከቤተ መቅደሳችን አውጥቶ ጣለ:: አንዱን ዝቅ ሌላውን ከፍ በማድረግ የውስጡን ሲኖዶስ በውጩ ካለው ሲኖዶስ ጋራ አጋጨ:: የቆመባትን የዋሸንግተን ቅድስት ማርያም ቤተ መቅደስ ከጠቀሳቸው ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት ጋራ አጋጨ:: ግራና ቀኝ በማየት፥ አርቆ በማሰብ፥ በነገረ መለኮቱም ሆነ እሱ ተማርኳቸው በሚላቸው የእውቀት ዘርፎች ከሱ ቀድመውና ርቀው የሄዱትን የካንሳስ መድኃኔ ዓለምን ምእመናን ላይም፥ *“መገንዘብ፥ ማወቅ፥ ማስተዋልና መረዳት ይገባቸዋል”* እያለ የስግ-በለው አሽሙሩን ረጨ:: በቅዱሳን አበውና የየራሳቸውን ትውፊት ጠብቀው በመስመራቸው ቆመው ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ላይ ለማንደድ ከዶግ አመድ ውስጥ እሳት ሲጭር፥ ከነደደ የማይጠፋ ግለቱ የማይበርድ እሳት የሚያመነጨውን እቶን በራሱ ላይ እንዲነድ ቆሰቆሰ:: “ብእሲ አብድ ይከሪ ለርዕሱ እከየ:: ወውስተ ከናፍሪሁ ይዘግብ እሳተ”( ምሳ ፲፮፡፳፯) ያለው ይህን ለመሰለ ደፍተራ ገለፈት ነው:: ፊደል ቆጥሬአለሁ ነገረ መለኮት፥ ሳይኮሎጂ፥ ፊሎሶፊ ኢኮኖሚክስ አጥንቻለሁ፥ ርዕሰ ደብር ነኝ፥ ካህን ነኝ፥ የሚል ሰው ቀርቶ፥ ፊደል ያልቆጠረ ሰው ከመሬት ተነስቶ ይህን የመሰለ ስሕተት አያደርግም:: ይህን ፍርድ ላንባቢ፥ ለተመልካች፥ ይልቁንም ለቤተ ሰቡና ለቅርብ ጓደኞቹ እሰጣለሁ::

ጥበበኛው “አክሊለ ምክህ ርስዕ ሠናይ፥ ወውስተ ፍናወ ጽድቅ ይትረከብ”(ምሳሌ ፲፮፡፴፩) እንዳለው፥ ማለትም ሊያምኑት ምሳሌነቱን ሊከተሉትና ሊመኩበት የሚገባ ሽምግልና፥ እውነትን፥ ጽድቅንና ትክለኛ ፍትሕን ከመከተል ዝንፍ ያላለ ሽምግልና ነው:: በዚህ መለኪያ የተቀረጸ ሽምግልና የሌለው ኅብረተ ሰብ፥ ዛፉ የተጨፈጨፈበት፥ ቅጽሩ የፈረሰበት አምባ ነው:: የዚህ አይነት ሽምግልናቸውን ይዘው መቃብር የገቡትን አባቶች ስንጠራቸው የሚሰሙን ስንቀስቅሳቸው የሚነሱልን ቢሆን፥ አየር በምንስብባት ደቂቃ ሁሉ ስማቸውን መጥራት ባልሰለቸን ነበር:: ይልቁንም የአካላቸውና የድምጻቸው ትዝታ የራሳችንን ባዶነት እየቀሰቀ እንባችንን እንድናፈርስ እያደረጉን ነው:: ይሁን እንጅ በአካል ቢለዩንም ትተውልን በሄዱት ቅርስ ሞቱ፥ ተለዩን አንልም:: በእድሜ በእውቀት በልምድ የበለጸጉ በሕወት ያሉ አባቶች አክሊሎቻችን ናቸው:: በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውና በዓለም ዙሪያ ተበትነን የምንኖር ሁሉ እንደቅርስ ማየት የሚገባን ጥቂት አባቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: ከነዚህ ውስጥ አንዱ በመካከላችን በሕይወት ያሉት አባት ዶክተር አክሊሉ ሐብቴ ናቸው:: የሞራል፥ የመንፈስ፥ የሃይማኖት፥ የታሪክ ጥማት ለገጠመው ሁሉ ዜጋ ከምሳሌነታቸው ጠጥቶ እንዲረካ መጋበዝ ከሚችሉበት አፋፍ ላይ የተቀመጡ ናቸው፥ ብየ አምን ነበር::

ይህ ታላቅ ዕድል እያላቸው፥ ነገረ መለኮትን ታሪክን ቤተ ክርስቲያንን የሚንድ ጉድ የተሸከሙትን ጠልሳሚ ጥሩ የተዋጣለት ደራሲ፥ ጠልሰሞችን የጠራ ትምህርት ሰጭ አድርገው የተቀደሰውን አውደ ምሕረት የጠልሰሞች መሸጫ ገብያ በማድረጋቸው የነበረኝን ግምት

አንኮታኮቱት::ከዜግነታቸው፥ ከእድሜያቸው፥ ከምሁርነታቸው፥ ከደለበው ልምዳቸው አንዱ እንኳ ይህን ስህተት ሲፈጽኑ ሕሊናቸውን ሳይገስጸው መቅረቱ እንቆቅልሽ ሆነብኝ:: ፍርዱን ለተመልካች እተወዋለሁ

አቶ ቢልልኝም ከዚህ ቀደም እንደዛሬው ንስሐ ገብቻለሁ፥ እዘምራለሁ፥ እቆርባለሁ፥ የነገረ መለኮት መጽሐፍ አርማለሁ ከማለታቸው በፊት፥ የነበረውን ሕይወታቸውን ለወገን ለሀገር ምን እንደሰሩ ከሞላ ጎደል ግልጫለሁ:: በአሁኑ ሕይወታቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ሽቅብ ቁልቁል ከፍና ዝቅ እያደረጉ ይመዝኑበት የነበረው እንደ ጃንጥላ የታጠፈባቸውን ሥልጣን አጥተው በስደት ባሉበት ጊዜ፥ ከሳቸው ጋራ የነበሩት ጓዶቻቸው ግማሾቹ በሞት ግማሾቹ ከሞት በታች እንዳሉ ጭራሽ ረስተውታል:: እውነት የተዋሕዶ ክርስትና አማኝ ቢሆኑ፥ አሁን ያሉበት ቦታና እድሜ ለንስሐ ለርህራኄ ለይቅርታ ለሽምግልና ለጸጸት የተመቸ ታላቅ እድል ነበር:: ሆኖም በአፋቸው ንስሐ ገባሁ ቀረብኩ ይላሉ እንጅ አሁን የሚሰሩት ከሃይማኖት ውጭ በነበሩበት ጊዜ ከሰሩት እጅግ የከፋ ነው:: ይህን ለማለት ያበቃኝ፥ *"ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት"* እና "ክርስቶስ ፍጡር ወይስ ፈጣሪ" በሚል አርስት በጠለሰማቸው እስካሁን የገለጽኳቸው ወደፊትም የምንሄድባቸውን ክህደቶች ያላንዳች ውልውል በድፍረት ከሚቀባዥር ደፍተራ ገለፈት ጋር መሰለፋቸው ነው:: በአራችን ያጠራቀሙት ልማትም ሆነ ጥፋት ከስደት ኑሯቸው ጋራ ተደምሮ፥ ከደፍተራ ገለፈት ጋራ የፈጸሙትን ስሕተት ልክ አለመሆናቸውን እንዴት ሊያሳያቸው አልቻለም? ተመልካች ወገን፥ ይልቁንም ቤተ ሰቦቻቸው፥ እግዚአብሔር በሚቀበለው ከወገናዊነት በተላቀቀ ሕሊና ይፍረዱ!

ወደ ረቀቀችውና ወደ እማትሞተው ነፍሳችን እንመለስና፥ ሁላችንም በእግዚአብሔር እናምናለን:: ቢያንስ የጸሐይ መውጣትና መጥለቅ፥ የወጣንበትን የእናቶቻችን ማሕጸንና በመጨረሻም የምንገባበትን መቃብር እንድናስታውስ ያሳስበናል:: የዚህ ሥርዓት ባለቤት በሆነው ፈጣሪ ፊት ለደቂቃ ያህል እንድንበረከክ ያስገድደናል:: ቅዳሴያችን "እመቦ ዘወድቀ በኃጢአት ኢይርሳ እስመ ዘኢይትረሳ" እንዲል፥ ማለትም፡- "በስሕተት የወደቀ ሰው፥ መጸጸት እንዳለበት አይርሳ፡ ከተጸጸተ በኋላም ተመለሶ እንዳይወድቅ አይርሳ" ሲል መጽሐፈ ቅዳሴያችን ያዝዛል:: በትእዛዙ መሠረት የተሸከምነውን እዳና በደል ከራሳችን ሳናወርድ ሥጋውን ደሙን ለመቀበል እሁድ እሁድ ወደ ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ ስሕተት ነው:: የተሸከምነውን በደል በኑዛዜ ከራሳችን ሳናወርድ ወደ ቁርባኑ መምጣት ቀርቶ፥ ከላይ እንዳልኩት ይቅርታ ለመጠየቅ የጸሐይ መጥለቅ ልትቀድመን አይገባም:: ከደፍተራ ገለፈት ጋራ ተባብራችሁ የፈጸማችሁትን በደል ተሸክማችሁ ወደ ቁርባኑ መቅረብ ቀርቶ፥ በሕዝበ ክርስቲያኑ መካከል በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቆሞ መታየት ከክርስትናችን ውጭ ነው:: ስለዚህ በዚያው በደሉን በፈጸማችሁበት አውደ ምሕረትና ሕዝብ ፊት ይቅርታ እንድትጠይቁ እጠየኩ ወደ መደምደሚያየ እሻገራለሁ::

# ማጠቃለያ

እስካሁን ድረስ ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የመጣው ትምህርት፥ ወደ ቤተ ክርስቲያናች መግባት የለበትም በማለት መጀመሪያ አገር ቤት ላለው ሲኖዶስ ከዚያ መልስ ባለማግኘታችን ጉዳዩ እነሱንም የሚመለከታቸው ስለሆነ ለአኅት አብያተ ክርስቲያናት አቅርበናል::

ሁሉም ኦርቶዶክሳውያን የሚጸየፉት ይህ ትምህርት ወደ እኛ ቤተ ክርስቲያን በመግባቱ አዝነው የግብጽ ቤተ ክርስቲያን በጽሑፍና (Read the leter here http://www.medhanialemeotcks.org/pdf/HG%20Bisop_David-Letter.pdf ) በአካልም በመካከላችን ተገኝተው፥ በርቱ ጠንክሩ! በያዛችሁት ትምህርትና እምነት ጽኑ! እኛም ከጎናችሁ ቆመናል! በማለት አጽናንተውናል:: የሶርያው ሊቀ ጳጳስም በነገሩ እጅግ አዝነው፥ በኒዮርክ ያሉትን አቡነ ዘካርያስን አነጋግረዋል:: አቡነ ዘካርያስም "ሲኖዶሱ ጉዳዩን እያየው ነው ብለው ተናገሩ:: ያንተ አቋም ምንድነው ተብለው ሲጠየቁ አቋማቸውን መግለጽ አልፈለጉም፥ እኔ እንዲነጋገርባት ለራሴ ሲኖዶስ አቀርባለሁ:: በያዛችሁት በኦርቶዶክስ እምነታችሁ ጽኑ፥ የእመቤታችን ረድኤት ከናንተ ጋር ይሁን" ብለው የመለሱላቸውን ጠቅሰው የጻፉልን ደብዳቤ በጽሕፈት ቤታችን ይገኛል:: ይህን በተመለከተ የመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በቅርቡ የሚሰጡት መግለጫ ይኖራቸዋል::ጉዳዩ በዚህ እያለ፥ ደፍተራ ገለፈት ከጥንተ አብሶ ትምህርት እጅግ የባሰና የከፋ፥ ጨርሶም ቤተ ክርስቲያናችንን የሚያዋርዱና ሕዝቡን የሚያደናግሩ *"ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት"* እና *"ክርስቶስ ፍጡር ወይስ ፈጠሪ"* በሚል ሁለት የተለያዩ የክህደት ጠልሰሞችን አዘጋጅቶ አሰራጨ::

ቅዱሳን ሊቃውንት አበውን አዋርዶ፥ መጻሕፍቶቻችንንና ታሪካችንን ንቆና አቃሎ፥ ቤተ ክርስቲያናችን የተጓዘችበትን የጨለማ ጉዞ አድርጎ በመቁጠር፥ የሮማ ካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን እንድንከተል እያለ ሳያወላውል በማቅረቡ፥ በፈጸመው ስሕተት ተጸጽቶ እስኪመለስ፥ መጻሕፉትም እስኪታረሙ ድረስ፥ የተዘለፉ ኦርቶድክሳውያን አብያተ ክርስቲያናትና ከፍና ዝቅ እያደረገ ያቀረባትን የሮማ ካቶሊክን ቤተ ክርስቲያን ይቅርታ እስኪጠየቅ፥ ከቤተ መቅደስ እንዳይገባ በመላ ኦርቶዶክሳውያን እማኝነት ስጠይቀው የዲሲ ቅድስት ማርያምና ቦርዱ ጥያቄዬ ተገቢ መሆኑን እንደምትቀበሉት እርግጠኛ እሆናለሁ:: እነዚህ እስኪፈጸሙ ድረስ፥ የዲሲ ቅድስት ማርያምን አውደ ምሕረት መነኻ እያደረኩ የሚጠቀሱትን ሰዎች በመጥቀስ ከዚህ በታች በዝርዝር በምጠቅሳቸው አንቀጾች የማዘጋጃቸውን እያከታተልኩ እንደማቀርብ ከወዲሁ መግለጽ እወዳለሁ::

*"ክርስቶስ ፍጡር ወይስ ፈጣሪ"* በሚል ርእስ ያቀረባትን ጠልሰም አንብቤ በ *"ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት"* ካገኘናቸው ስሕተቶች እጅግ የከፉ ስሕተቶችን እንደያዘች ተረድቻለሁ:: ይሁን እንጅ *"ማርያማዊ ሕገ ሃይማኖት"* ከደረስኩባቸውና የማዘጋጃቸው ጦማሮች የሚዳስሷቸው አሉኝ ከምላቸው ብዙዎች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው::

፩ኛ. *“ከእመቤታችን የተወለደው ሩቅ ብእሲ ሳይሆን ባንድነትና በሶስትነት የሚኖር ረቂቅ አምላክ መሆኑ ነው”* (ገጽ 125)

፪ኛ. *“የእግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን በሥላሴ ፈቃድና ኃይል ብቻ ሳይሆን በድንግል ማርያም ትብብርና ስምምነት ጭምር ነው”* (ገጽ 110)::

፫ኛ. *“እነሆ የጌታ ባሪያ እንደቃልህ ይሁንልኝ፥ በማለቷ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋ ለብሶ ዓለምን የሚያድንበትን ሁኔታ አመቻቸችለት*

፬ኛ. *“የድንግል ማርያም ትብብር ወሳኝ በመሆኑ በክርስቶስ የማዳን ሥራ ተካፋይ ናት”* . . . .
አባሪ አዳኝ ናት፥ (ገጽ 106)

፭ኛ. *“አምላክ በባሕርይ ሰው ሆነ፡፡ ሰውም በጸጋ አምላክ ሆነ”* (ገጽ 121)

፮ኛ. *“በግልጽ ወለደችው፥ በታላቅ ኃይል አስገኘችው፥ በቸርነት ጠበቀችው፥ በግርማም ገለጸችው”* (ገጽ 146)

፯ኛ. *“ማርያም ሶስት ወር ያህል ከዘመዷ ቤት ከርማ ወደ ቤቷ ስትመለስ የሚጠብቃትን ስለማታውቅ ሥጋት ሳያድርባት አልቀረም”* (ገጽ 13)

፰ኛ. *“በቤተ መቅደስ ሳለች የድንግልና ሕይወት ለመኖር መኃላ ፈጽማለች ተብሎ ስለሚታመን የደናግልና የመነኮሳት መመኪያ የሚል ቅጽል ተሰጥቷታል”* (ገጽ 169)

**አበው “ዘይህብ መርሀ ርቱዐ ለቤተ ክርስቲያን” እያሉ የሚጮሁለት አምላክ አበው ለቤተ ክርስቲያችን የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምቶ የሚያሰማን መሪ ያዘጋጅላት!!**

**ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ፥**

http://www.medhanialemeotcks.org/